# ሕዝብና አስተዳደር

## ሞራል

ከይድነቃቸው ተሰማ

በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ በሠላሳ ሁለተኛው ዘመነ መንግሥት

አዲስ አበባ ፲፱፻፶፬ ዓ ም

በአርቲስቲክ ማተሚያ ቤት ታተመ ቍ 7439



# ግ ር ማ ዊ ሆ ይ

ሕዝብና አስተዳደር የተባለችውን ይህችን መጽሐፍ ያዘጋ ጀሁት ዝቅተኛ አገልጋይዎ በተለምዶ ደራሲ አይደለሁም ። ምንም እንኳን ለልዩ ልዩ መሥሪያ ቤቶች ሥራቸውን ስለሚመለከቱ ጉዳዮች ብዙዎች መጽሐፎችና ደንቦች ባዘ ጋጅም ፥ በራሴ ስም ጠቅላላውን ጥቅም የሚመለከት መጽ ሐፍ እስካሁን አላዘጋጀሁም ነበረ ።

ሕዝብና አስተዳደር በተባለው አርዕስት ስር ለመጻፍ በሰፊ ያል ሳይንስ ፤ የበቃ ትምሕርት ማግኘት አስፈላጊ መሆኑን አውቃለሁ ። ቢሆንም ልዩ ልዩ መጽሐፍት በማንበብ ራሴ ለመረዳት የቻልኩትን ያህል ሌሎችም ቢያውቁ የሚጠ ቅም መስሎ ስለታየኝ ለማዘጋጀት ደፍሬያለሁ ።

ኢትዮጵያ ከግርማዊነትዎ በተሰጣት ሕገ መንግሥት መሠረት የምትተዳደር መሆኗ ብዙ ጊዜ የተነገረና የተገ

ለጸ ቢሆንም ፤ አብዛኛው ሰው ሕገ መንግሥት ማግኘቱ ዋጋው የቱን ያህል እንደሆነ እንደሚበቃ ለማወቅና ለመገንዘብ ገና ባለመቻሉ ተገቢውን ግምት አልሰጠውም ፤ ስለዚህ ዋናው ዓላማዬ ሕዝቡ በሕገ መንግሥቱ የታወጀውን በዝርዝር ለመረዳት እንዲችልና ሕገ መንግሥቱ በሰጠው መብት እንዲሠራበት ፤ የተጣለበትን ተግባር እንዲፈጽምና የግርማዊነትዎ ውለታ የቱን ያህል እንደሆነ እንዲያውቀው ነው ።

በራሴ በኩል ግን መጽሐፉን ራሱን ሳዘጋጅ ምኞቴ የቀድሞዎቹ ነገሥታት ያላደረጉትን ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቀረብኝ ብሎ ያላሳሰብዎትን ፣ ሊነሱት ችሎታ ሲኖርዎ በፈቃድዎ ለመጀመሪያ ጊዜ ለሕዝብዎ ሕገ መንግሥት በመስጠትዎ ፍጹም አድናቂና ባለውለታ መሆኔን ለመግለጽ ነው ።

ይድነቃቸው ተሰማ

# ማስተዋወቂያ

እንባቢ ሆይ ፤

የዚህ መጽሐፍ ዓይነተኛ ዓላማ ምን እንደሆነ በመጀመሪያው ገጽ ላይ አስረድቻለሁ ። ሕዝብና አስተዳደር ፣ ሕገ መንግሥት ፣ ለያንዳንዱ ሰው የሰጡት መብት ብቻ ሳይሆን ተግባርም ጭምር ነውና በተሰጠው መብት መጠቀም የሚመኝ ሁሉ ለውጡን የተጣለበትን ተግባር መፈጸምም መልመድ አለበት ።

የመጽሐፉ አቀራረብ ቀጥሎ በተመለከተው አኳኋን ነው ።

መጽሐፉ በሁለት ላይ ተከፍሏል ፣ መጀመሪያው የሕዝብና የአስተዳደርን ሁኔታ ሲይዝ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ በተለይ ስለሞራል የተዘጋጀ ነው ።

ሃሳቤን በቂና አጥጋቢ በሆነ መንገድ ለመግለጽ በማሰብ ያልተለመዱ ወይም አዳዲስ ቃላቶች በጽሑፉ ውስጥ ለማግባት ተገድጃለሁ ። ስለዚህ ከዚህ በሚከተለው ገጽ የነዚህን ቃላቶች ዝርዝር በፊደል ተራ ባማርኛ ፣ እጐኑ ተመዛዛኙን የውጭ ቃልና ፣ ሶስተኛ የቃሉን ፍች የሚያስረዳ ሰሌዳ አዘጋጅቼለታለሁ ።

የመጽሐፉ መጀመሪያ ክፍል በስድስት ምዕራፎች ተከፍሏል ።

አንደኛው ስለሕዝብና ስለ መንግሥት ፣ ሁለተኛው የኢትዮጵያን ሕገ መንግሥትና የሥልጣንን አከፋፈል ፤ ሶስተኛው ስለ ግዛቶች አከፋፈል ፣ አራተኛው ስለ ከተሞችና ስለማዘጋጃ ቤቶች ፣ አምስተኛው ስለሚኒስቴሮች ፣ ስድስተኛው ፣ ስለአገረ ሰብ መብትና ተግባሮች ያትታሉ ። በጠቅላላውም የነዚህን ድርጅቶች ዓላማ ፣ አቋቋማቸውንና ፣ የሕዝቡንም ተካፋይነት ጭምር ግልጽ በሆነ መንገድ ለማስረዳት ሞክሬያለሁ ።

በሁለተኛው ክፍል ደግሞ ፣ በሞራል ረገድ ሰው የሚመራባቸውን ፣ ሕጐች በዘጠኝ አንቀጾች በመክፈል ፣ ማለትም 1 ተጠያቂነት ወይም አላፊነት ፣ 2 (ግብረ ዋጋ) ቅጣት 3 ተባባሪነት 4 ግለ ሰብ 5 ቤተ ሰብ 6 ሕዝብ 7 አገር 8 መንግሥት 9 ኤኰኖሚካዊ ኑሮ በሚሉ አርዕስቶች ነጣጥዬ አዘጋጅቼዋለሁ ።

ኢትዮጵያውያን አንባቢዎች ፣ የሚያውቁትም በሃሳቡ እንዲስማሙበት ፣ ከዚህ ቀደም የማያውቁትም ፣ ጠቃሚ ነገሮች እንዲያገኙበት ተስፋ አደርጋለሁ ።

አ ዘ ጋ ጅ ው

መጽሐፉን ለማዘጋጀት የጠቀሙኝን የፈረንሣይ መጻሕፍት ለጠቆሙኝና ለረዱኝ ፣ ለሊሴ ገብረ ማርያም ዲሬክተር ለሙሴ ቤርላንና ለሙሴ ኰምባ ጥልቅ የሆነ ምስጋና አቀርባለሁ ፤

# ማ ው ጫ


1 ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ፣ ማቅረቢያ ።

2 ማስተዋወቂያ ።

3 ማውጫ ።

4 የቃሎች ፍች ።

5 ሰውና አስተዳደር ።

6 ምዕራፍ 1 ሕዝብና መንግሥት ።
  ሕዝባዊ ጸጋዎች ።

7 ምዕራፍ 2 የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥትና የሥልጣኖች አከፋፈል ።
  ሥልጣን የተለየበት ምክንያት ።
  ሕግ አስፈጻሚ ሥልጣን ።
  ሕግ አውጭ ሥልጣን ።
  የዳኝነት ሥልጣን ።

8 ምዕራፍ 3 የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ግዛት አከፋፈል ።

9 ምዕራፍ 4 ከተሞችና ማዘጋጃ ቤቶች ።
  የካርታ ክፍል ።
  በከተማ ውስጥ የጸጥታ ጥበቃ ።
  ትምህርት በከተማ ውስጥ ።
  ተራድኦ በከተማ ውስጥ ።
  ስለ ማሕበሮች መቋቋም ።

**ተ**

**24. ተባባሪነት** Solidarité

ሰው አንዱ ለሌላውና በሌላው እንደሚኖርና እኩሉ ተከፍቶ እኩሉ ሊደሰት የማይችል ፍጡር መሆኑን የሚያስገነዝበን ስሜት ነው ፤

**25. ተራድኦ** Assistance

ላልተመቻቸው ለመርዳት የተቋቋመ ድርጅት ነው ፤

**26. ተግባር** Devoir

ልንፈጽመው ግዴታ የሆነ ሥራ ፣ ግዳጅ ፤

**27. ታህተምድር** Sous - Sol

ከምድር ቅርፊት በታች ያለው ሁሉ ፤

**28. ትረስት ፤** TRUST

ሰብስቦ በመያዝ ያንድን ገንዘብ አቅዋም ወይም ያንድን ሸቀጥ ዋጋ ከፍ ለማድረግ የሚቋቋሙ ፣ ድርጅቶች ናቸው ፤

**ዓ**

**29. ዓለምአቀፍ** Universel

በጠቅላላ ዓለምን የሚመለከት ፤

**30. አሐዱነት** Unité

አንድ የመሆን ባሕርይ ፤

**31. አክባጅ** Aggravant

ጥፋትን ይበልጥ ከባድ የሚያደርግ ሁኔታ ፤

**32. አገረሰብ** Citoyen

ያንድ አገር አባል የሆነ ሰው ፣ (መብትና ተግባር ያለው)

**33. አቃላይ** Atténuant

ጥፋትን ይበልጥ የሚያቃልል ሁኔታ ፤



**34. አንድ ጋብቻ** Monogamie

ወንድ ካንዲት ሴት በቀር ፣ ሴት ካንድ ወንድ በቀር ለማግባት የማይችሉበት ሥርዓት ፤

**ወ**

**35. ወግለበስ** Solennel

በታላቅ ክብርና ሥርዓት የሚፈጸም ነገር ፤

**ዘ**

**36. ዘመንጓድ** Contemporains

ባንድ ዘመን ውስጥ የሚኖሩ ፤

**ዶ**

**37. ዲክታተር ፤** Dictateur

ሥልጣንን ሁሉ በጁ የሚጨብጥ ፤

**38. ዲፕሎማሲ** Diplomatie

ኢንተርናሺናል ግንኙነቶችን የማወቅ ጥበብ ፤

**39. ዲሞክራሲ** Démocratie

በሕዝብ ፈቃድ የመተዳደር ዘዴ ፤

**40. ድሕረሞት** Outretombe

ከሞት በኋላ ፤

**ግ**

**41. ግለሰብ** Individu

ከተመሳሳይ ፍጥረቶች አንዱ ፣ በኛ መጽሐፍ ከሰዎች መካከል አንዱ ማለት ነው ።

3 ዲክታተራዊ ግዛት ፤ በትውልድና በውርስ ወይም በመ
መረጥ ሳይሆን ፤ ያስተዳደር ሥልጣን ፣ በኃይል በያ
ዘው ባንድ ሰው እጅ ብቻ ሲሆንና ፣ ያለተቆጣጣሪ ሊሠ
ራበት ሲችል ፤ አገሪቱ በዲክታተር ትገዛለች ማለት
ነው ።

4 ሪፐብሊክ ፤ በመሠረቱ ፣ ሕዝብ በመረጠው ፕሬዚዳ
ዳንት የማስተዳደር ዘዴ ነው ፤ በፕሬዚዳንትትና በንጉሥ
መካከል ያለው ልዩነት ፣ ፕሬዚዳንቱ ሥልጣኑን የሚይ
ዘው በመመረጥና ለተወሰነ ጊዜ ብቻ ሲሆን ፤ ንጉሡ
በውርስና ለዕድሜ ልኩ መሆኑ ብቻ ነው ። ዴሞክራቲ
ካዊ ግዛተ ዘውድና ዴሞክራቲካዊ ሪፐብሊክ ፤ በጣም
የተመሳሰሉ ያስተዳደር ዓይነቶች ናቸው ፤

ዴሞክራሲ ማለት ፤ ሕዝቡ በመንግሥቱ አስተዳደር ተካ
ፋይ የሚሆንበትና ፤ ባብዛኛው ክፍል ውሳኔ የሚተዳደር
በት ዘዴ ነው ። ሕዝቡም በቀጥታ ራሱ ፤ ተሰብስቦ ውሳኔ
ለመስጠት ብዛቱ ስለማይፈቅድለት ፤ በሱ ስም ሆኖ ሃሳቡ
ንና ፤ አስተያየቱን የሚገልጽ እንደራሴ ፣ በድምጽ ብልጫ
መርጦ ይሾማል ፤ (የሕዝብ እንደራሴዎች)

## ሕዝባዊ ጸጋዎች (ጤናነት)

በአገራችን የሕዝብ እንደራሴዎች መምረጥ በ1948 ዓ ፡ ም ፣
ተጀመረ ።
እንደራሴ መምረጥ ማለት ፤ በኔ ስም ሆኖ ስለአገሪቱ አስተ



ዳደር ሕጎች በሚደረጉ ጥናት ላይ አስተያየት የሚሰጥና
መብቴን የሚጠብቅልኝ ሰው ማድረጌ ነው ፤

እንደራሴ መምረጥ ለአገረ ሰብ የተሰጠው ታላቅ መብት
ነው ። ነገር ግን ምርጫ ፣ በሚደረግበት ጊዜ ሁሉ ብዙዎቹ
ግዴታ የለብንም በማለት ድምጽ ሳይሰጡ ይቀራሉ ። ከ
ብዙ ሺ ዓመቶች በኋላ በተሰጠው በዚህ ታላቅ መብት አለ
መጠቀም ፤ አላዋቂ ያሰኛል ። ባይሆን ፣ ለመመረጥ ከቀረ
ቡት እጩዎች መካከል ፣ የምንፈቅደው አንድም ባይኖር ፤
በሳጥኑ ውስጥ ነጭ ወረቀት መጣል ይሻላል ።

እንደዚህ በምናደርግበትም ጊዜ በጉዳዩ ላይ ያለንን አስተያ
የት መስጠታችን ነውና ድምጽ እንዳልሰጠን አይቆጠርብ
ንም ። የሚያሳዝ ነው ግድ የለሽ ሆኖ አስተያየት አለመስ
ጠቱ ነው ።

<u>ሕግን ማክበር</u> ፤ ሕግ አገርና ሕዝብ የሚተዳደሩበት ፣ የሰ
ላም ፣ የጸጥታ ፣ የእምነት ፣ መሠረት ስለሆነ ፤ እያንዳንዱ
ሰው ያለማመንታት ሊያስክብረው ይገባል ። ስለዚህ ማንኛ
ውም ሰው ፤ አንዱን ሕግ እኔ አልወደድኩትምና አልፈጽመ
ውም ሊል አይችልም ፤ አብዛኛው ክፍል የተስማማበት ከ
ሆነ ፣ ቢወዱትም ባይወዱትም ሕጉን መቀበልና ማክበር
የዴሞክራሲ ዋናው መሠረት ነው ።

ከሕዝባዊ ተግባሮችም መካከል በተለይ ሊታለፉ የማይ
ቻል ሶስት ነገሮች አሉ ።

— እያንዳንዱ አገረ ሰብ ልጆቹን ማስተማር ወይም
እንዲማሩ ማድረግ አለበት ።

# ሶስት ሥልጣኖች

ከ1923 ዓ ፡ ም ማለትም ከ30 ዓመታት በፊት ፣ አገራችን ኢትዮጵያ ትተዳደርበት የነበረው ፣ ደንብና የገዥዎች ሥልጣን ፣ ዝክረ ነገር ፣ ተብሎ በተሰየመው ክቡር ባላምበራስ ማሕተመ ሥላሴ ። ባዘጋጁት መጽሐፍ ተዘርዝሯል የዚህ መጽሐፍ ዓላማ ፣ በ1948 ዓ ፡ ም ፡ በተሻሻለው ሕገ መንግሥት መሠረት ብቻ ያገራችንን አስተዳደር ዘርዝሮ መግለጽ ነው ።

## ሥልጣን የተለየበት ምክንያት

— መብት መጠበቁን የሚያረጋግጥ ዋስትና የሌለበትና ፣ ሥልጣን በሕግ ያልተለየበት ማሕበር ፣ ሕገ መንግሥት አለው ለማለት አይቻልም ።

<u>ምሳሌ ።</u> የሕዝብ እንደራሴዎች ትምሕርት ግዴታ ነው የሚል ሕግ ያወጣሉ ።

ይህ <u>የሕግ አውጭ ሥልጣን</u> አድራጐት ነው ።
የወጣውን ሕግ ማስፈጸም ፣ መከበሩን መቆጣጠር ፣ ሕግ የሚተላለፉትን ። መያዝ ። ያስፈልጋል ፣ ይህ በመንግሥቱ በኩል ይፈጸማል ።

ስለዚህ <u>አስፈጻሚ ሥልጣን</u> ይባላል ።



አስፈጻሚው ሥልጣን ፣ ጥፋተኞች ከያዘ በኋላ ፣ ራሱ ሊዳኛቸው አይችልም ።

እፍርድ ፊት ያቀርባቸዋል ። ዳኛውም ተከሳሹ ሕግ መጣሱን አለመጣሱን ። አስቀድሞ ካረጋገጠ በኋላ ። ይበይንበታል ወይም ነጻ ያወጣዋል ። ይህ <u>የዳኝነት ሥልጣን</u> አድራጐት ነው ።

እነዚህ ሶስቱ ሥልጣኖች ያልተለያዩ እንደሆነ ለምሳሌ ያህል ቀጥሎ የተመለከቱት ነገሮች ሊደርሱ ይችላሉ ።

1 አስፈጻሚው ባለሥልጣን ፣ ትምሕርት ግዴታ ነው የሚል ሕግ ራሱ ያወጣል ። በጉዳዩ ላይ የሕዝቡን ፣ ማለትም በምክር ቤት የሕዝብ እንደራሴዎችን አሳብ አልጠየቀምና ሕጉ በሕዝቡ አብዛኛው ክፍል የተደገፈ ለመሆኑ ። እርግጠኛ ሊሆን አይችልም ። በዴሞክራሲ መንፈስ ይህ ሕግ ዋጋ ሊኖረው አይችልም ።

2 አስፈጻሚው ሥልጣን ፣ ሕግን በሚያስፈጽምበት ጊዜ ፣ አንድ ሕግ ተላላፊ አግኝቶ ይይዛል ። ከዚያም በኋላ ጉዳዩ እንዲፋጠን በማለት ራሱ ቢዳኘውና ቢፈርድበት እራሱ ከሳሽ ፣ እራሱ ዳኛ መሆኑ ነውና ሕጋዊ ድርጊት ሊሆን አይችልም ።

3 ሕግ አውጭው ሥልጣን ደግሞ ፣ ሕግን እራሴ አስከብራለሁ ብሎ ቢነሳ ፣ ሊያደርገው የሚችልበት ዘዴ የለውም ። የፖሊስ ኃይል ከሌለው ፣ እያንዳንዱ የፓርላሜንት አባል ፣ ራሱ ፖሊስ ሆኖ ወንጀለኞች ሊያሳድድ

አይችልም ። ስለዚህ የሕግ አስፈጻሚ ሥልጣን መኖር በግድ አስፈላጊ ነው ።

ይህ አጭር ምሳሌ የሶስቱ ሥልጣኖች መለየት ላንድ አገር ፍጹም አስፈላጊ መሆኑን ያሳዩናል ።

## ሕግ አስፈጻሚ ሥልጣን

በኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት ፥ የሕግ አስፈጻሚነት ሥልጣን የተሰጠው ፥ የሕዝቡ መሪ ለሆነው ለንጉሠ ነገሥቱና በሕጉ መሠረት ሥራውን ለሚያከናውኑ ሚኒስትሮች ነው ። የሚኒስትሮችን ምክር ቤት የሚቆጣጠረው ሕግ አውጭው ሥልጣን ነው ።

**ንጉሠ ነገሥቱ ፤**

የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ዘውድ ከንግሥት ሳባና ከሰሎሞን ከተወለደው ፥ ከቀዳማዊ ምኒልክ ነገድ ሳይቋ ረጥ ተያይዞ ከመጣው ከንጉሥ ሣህለ ሥላሴ ፥ ዘር ከቀዳ ማዊ ኃይለ ሥላሴ ፥ ትውልድ የማይወጣ ነው ።

የዘውድ አወራረስ ተራ መስመሩን ይከተላል ፤ ይኸ ውም ከሕጋዊ ጋብቻ የተወለደ ወንድ ብቻ ይወርሳል ማ ለት ነው ። ያቀዳደሙ ተራ በሕገ መንግሥቱ ተዘርዝሯል።

የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ፥ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳ ዊት ቤተ ክርስቲያን እንዲያምን ግዴታ ነው ።



ንጉሠ ነገሥቱ በመንግሥቱ ላይ ሙሉ ገዥነትና የበ ላይም ሆኖ በአገሩ ጉዳዮች ላይ ፥ ከፍተኛ ሥልጣን አለው ።

የመሥሪያ ቤቶችን ባለሥልጣኖች መሾም ፥ በማዕረግ ማሳደግ ፥ ማዛወር ፥ መሻር የንጉሠ ነገሥቱ የተለየ መብት ነው ።

የማዘጋጃ ቤቶች ምክር ቤቶች መርጠው ከሚያቀርቡ ቸው ሶስት ሰዎች መካከል ፤ የከተማውን ማዘጋጃ ቤት ገዥ የሚሾም ንጉሠ ነገሥቱ ነው ።

ፓርላሜንቱ እየተስማማበት ፥ ጦርነት ለማወጅ መ ብት አለው ።

የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥም እንደመሆኑ መጠን ፥ ለመኰንኖች ማዕረግ መስጠትና ማሳደግ የንጉሠ ነገሥቱ መብት ነው ።

ከውጭ አገር ጋር የሚደረግን ግንኙነት የበላይ ሆኖ ይመራል ፤ አምባሳደሮችና ሚኒስትሮች እየሾመ የሚልክ ንጉሠ ነገሥቱ ነው ። እንዲሁም ከውጭ አገር የሚመጡ ትን መልክተኞች የሹመት ደብዳቤያቸውን የሚቀበል እሱ ነው ።

ኢትዮጵያ ከሌሎቹ አገሮች ጋር የምታደርገው ስምም ነት ንጉሠ ነገሥቱ ካልፈቀደ ሊጸድቅ አይችልም ።

ይህን የመሳሰሉትን ስምምነቶች በጠቅላላው ሁለቱ ምክር ቤቶች ከተስማሙባቸው በኋላ ፤ ለንጉሠ ነገሥቱ ይቀ ርባሉ ።

ንጉሠ ነገሥቱ የመስፍንነትና ሌላም ክብር ለመስጠትም ፥ ለመንሣትም ፥ አዲስ ኒሻን ለማውጣትም መብት አለው ።

ገንዘብ እንዲቀረጽ ፥ እንዲታተምና እንዲወጣ ማድረግ የንጉሠ ነገሥቱ መብት ነው ።

የፓርላሜንቱን ሁለቱን ምክር ቤቶች ለማፍረስና ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በአራት ወር ውስጥ መማክርቶች እንደገና እንዲሾሙ ፥ እንዲመረጡና እንዲሰበሰቡ ለማድረግ ይችላል ።

ንጉሠ ነገሥቱ የሕግ አሳቦች ለፓርላሜንቱ ለማቅረብ መብት አለው ።

ሕጎችና ድንጋጌዎች ዋጋ ኖሯቸውና ሊሠራባቸው የሚችለው ንጉሠ ነገሥቱ ተቀብሎ ካጠናቸውና ካሳወጃቸው በኋላ ነው ።

<u>መንግሥት ፤</u>

የመንግሥቱ ሥራ በንጉሠ ነገሥቱ የበላይ አዛዥነት ፥ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ሰብሳቢነት ፥ በሚመራ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይካሄዳል ፤

የመንግሥቱ አባል ባለሥልጣን የሆነ ሰው ሌላ የግል የተለየ ሥራ ወይም ውክልና ሊኖረው አይችልም ፤ ለምሳሌ ባንድ ጊዜ የንግድ ሚኒስትርና ነጋዴ ለመሆን አይፈቀድም፤

የሚኒስትሮች ዓላማና ተግባር ፤ በምዕራፍ 5 ተዘርዝሯል ።



# ሕግ አውጭ ሥልጣን

ሕግ የማውጣት ሥልጣን ለሁለት ምክር ቤቶች ተሰጥቷል ። እነርሱም ፥ ሕግ መወሰኛና ሕግ መምሪያ ይባላሉ ።

የሕግ መወሰኛ አማካሪዎች ከንጉሠ ነገሥቱ ይሾማሉ፤

የሕግ መምሪያ አማካሪዎች በሕዝብ ድምጽ ይመረጣሉ ።

አንድ ሰው ባንድ ጊዜ የሁለቱ ምክር ቤቶች አባል ሊሆን አይችልም ።

የፓርላሜንቱ አባሎች በሕግ የተወሰነላቸውን ደሞዝ ይቀበላሉ ። ፓርላሜንቱ ፥ የመማክርቶቹን ደሞዝ የሚያሳድግ ማናቸውንም ሕግ ያወጣ እንደሆነ ያሕግ ሊጸና የሚችለው ቀጥሎ የሚመረጠው ፓርላሜንት ከተሰበሰበ በኋላ ነው ።

የምክር ቤቱ አባሎችና ሚኒስትሮች በምክር ቤቱ ውስጥ ባቀረቡት ጽሑፍ ፥ ወይም ባደረጉት ንግግር ምክንያት አይወነጀሉም ፤ ይህ ውሳኔ አሳባቸውን ያለስጋት ለመግለጽ የሚችሉበት መብት ሰጥቷቸዋል ።

<u>የሕግ አሳብ አቀራረብ ፤</u> ፓርላሜንቱ ለመከራከርና ይሁን ብሎ ለመወሰን ፤ የሚችለው አስቀድሞ የሕጉ አሳብ ሲቀርብለት ነው ። የሕግ አሳብም ፤ ማንኛውም ሰው እንዲያቀርብ አልተፈቀደለትም ፤ በተለይ ንጉሠ ነገሥቱና ከሁ

ለቱ ምክር ቤቶች እንደኛው አስር ወይም ከአስር በላይ በሆኑ ፣ አባሎች የተደገፈ ሲሆን የሕግ አሳብ ማቅረብ ይችላሉ ።

የድምጽ አሰጣጥ ፤ ምክር ቤቶቹ ውሳኔ የሚሰጡት በድምጽ ብልጫ ነው ። የድምጾቹ ቍጥር እኩል የሆነ እንደሆነ፣ ፕሬዚዳንቱ ያለበት ወገን ያመዝናል ።

አስቸኳይ ሁኔታ ፤ አማካሪዎች በማይሰበሰቡበት ጊዜ፤ አስቸኳይጉዳይየተገኘ ወይምየቀረበእንደሆነንጉሠነገሥቱ ከሕገ መንግሥቱ ጋራየማይቃወሱ፣ሕግሆነው፤የሚሠራባቸውን ድንጋጌዎች ለማወጅ ይችላል ። በዚህ ዓይነት አኳኋን የወጡ ሕጎች ፓርላሜንቱ በሚሰበሰብበት ጊዜ ፣ ቀርበውለት ፣ የተቀበላቸው እንደሆነ እንዳሉ ይጸናሉ አለዚያ ፓርላሜንቱ ሳይቀበለው ከቀረበት ቀን ጀምሮ የጸኑ መሆናቸው ይቀራል ።

የሕዝብ እንደራሴዎች አመራረጥ ፤

አስቀድሞ የንጉሠ ነገሥቱ ግዛት ፣ ሁለት መቶ ሺ ሰው በሚገኝባቸው የምርጫ አውራጃዎች ፤ ይከፈላል ።

ከዚህም በቀር ሰላሳ ሺ የሚሆኑ ሰዎች የሚኖሩበት እያንዳንዱ ከተማ አንድ የሕዝብ እንደራሴ ይኖረዋል ።

ቍጥራቸው ከሰላሳ ሺ በላይ የሆነ እንደሆነ ፣ በተጨማሪው በየሃምሳው ሺ ሰው አንድ የሕዝብ እንደራሴ በተጨማሪ ይኖራቸዋል ።



ለምሳሌ ባንድ ከተማ 130.000 ሰዎች ቢኖሩ ፣ ለመጀመሪያው 30.000 ፣ ሰው አንድ የሕዝብ እንደራሴ ፣ በተረፈ ለተጨማሪዎቹ መቶ ሺ ሰዎች በየሃምሳው ሺ አንድ በማሰብ ሁለት እንደራሴ ይጨመርና በጠቅላላው ከተማው ሶስት እንደራሴ ይኖረዋል ማለት ነው ።

የሕዝብ እንደራሴ ለመምረጥ ዕድሜ 21 ዓመት እንዲሞላ ፣ በምርጫው አውራጃ አዘወትሮ ነዋሪና የምርጫ ሕግ የሚጠይቀው ችሎታ ያለው ፣ በትውልድ ኢትዮጵያዊ መሆን ያሻል ።

የሕዝብ እንደራሴ ለመሆን ፣ ዕድሜው ከ25 ዓመት ያላነሰ ፣ የታመነ ያገር ነዋሪ የሆነ በምርጫው ሕግ ከሚወሰነው ያላነሰ ተንቀሳቃሽ ንብረት ወይም ርስት ያለው ፣ በምርጫ ሕግ የተጠየቀው ፣ ለተመራጭነት የሚያስችለው መብት ያልተወሰደበት በትውልድ ኢትዮጵያዊ መሆንን ይጠይቃል ።

እሁለቱም ላይ በትውልድ ኢትዮጵያዊ ማለት ፣ ኢትዮጵያዊ ሆኖ የተወለደ ማለት ነው ።

ሲወለድ የሌላ አገር ዜጋ የነበረና ከተወለደ በኋላ የኢትዮጵያን ዜግነት ለማግኘት የቻለ ሰው ለመራጭነትም ለተመራጭነትም ተገቢ አይደለም ማለት ነው ።

የሕዝብ እንደራሴዎች የሚመረጡት ለአራት ዓመት ነው ።

<u>የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባሎች ፤</u>

በሕግ መወሰኛ ምክር ቤት ንጉሠ ነገሥቱ ለስድስት ዓመት የሚሾማቸው የሕግ መወሰኛ ፣ ምክር ቤት አባሎች ይገኙበታል ።

የፓርላሜንቱ ደንቦችና አሠራሮች ባጭሩ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ናቸው ።

ይህ ድርጅት ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚተዳደርበትን ሕግ የሚያጠናና የሚያወጣው አቅዋም ነው ፤ ከ1948 ዓ፡ም፡ ጀምሮ ሕዝቡ የሚመራበት ሕግ በሚወጣበት ሥራ ተካ ፋይ እንዲሆን ፤ መብት ስለተሰጠው እንደራሴዎቹን ፣ መ ርጦ ፣ በምክር ቤቱ ተገኝተው በሚጠቅመውና በሚጐዳው ነገር ላይ ተከራክረው ሕጉ እንዲወጣ ወይም እንዳይወጣ ለማድረግ በመቻላቸው ፣ ያላወቀውንና ያልተስማማበትን ሕግ እንደጥንቱ እንዲያከብር መገደዱ ቀረለት ።

ፓርላሜንቱ ፣ ማለትም <u>የሕግአውጭው ሥልጣን ፣</u> ዋ ናዎቹ ሥራዎች ፤ ሕግን ማውጣት ፤ አስፈጻሚውን ሥል ጣን መቆጣጠርና ፣ ባጀቱን ማጽደቅ ነው ።

ለባጀቱ የሚሆነው ገንዘብ ፣ አብዛኛው ፣ ሕዝብ ከሚከ ፍለው ግብርና ቀረጥ የሚሰበሰብ ስለሆነ ፤ አገባቡንና አወጣ ጡን ፣ ማለትም ባጀቱን ፣ የሕዝብ እንደራሴዎች መርምረው እንዲያጸድቁት መደረጉ ሕግን የተመረኰዘና ትክክለኛ አስ ተያየት ነው ።



# የዳኝነት ሥልጣን

በኢትዮጵያ አስተዳደር ሶስተኛው ሥልጣን የዳኝነት ሥልጣን ነው ፤ በሕገ መንግሥቱ ፣ የተሰጠው ደንብ ባጭሩ ቀጥሎ የተመለከተው ነው ።

— የዳኝነት ሥልጣን በሕግ ለተቋቋሙት ፍርድ ቤቶች የ ተሰጠ ነው ።

— ዳኞች በሕግ መሠረት ሲያነጋግሩና ፍርድ ሲሰጡ ነጻ ናቸው ፣ የፍርድ ሥራን በሚሠሩበትም ፤ ጊዜ ከሕግ በቀር በሌላ ሥልጣን አይመሩም ፤

— ዳኞችን የሚሾም ንጉሠ ነገሥቱ ነው ፤

ዳኝነት በሠለጠነ ሕዝብ አስተዳደር እንደፖሊስ አ ቋም ፣ ለማሕበራዊ ኑሮ በቅድሚያ የታሰበበት ድርጅት ነው ። በዛሬ ዘመን ሰው በገዛ ኃይሉ እንዲበቀል ወይም እን ዲካስ አይፈቀድም ፣ በሰዎች መካከል የሚነሱ አከራካሪ ነገሮች ሁሉ በትክክለኛና በሰላማዊ መንገድ በዳኝነት እን ዲታዩ ሥልጣኔ ያስገድዳል ።

በጥንት ዘመናት ፣ ሕዝቡ ተሰብስቦ ራሱ ይፈርድ ነ በረ ፤ ባንዳንድ አገሮች ባላባቱ ወይም ዕድሚያቸውና አስተ ዋይነታቸው የታወቀ ሽማግሌዎች ፍርድ ይሰጡ የነበረበት ጊዜ አለ ።

ነገር ግን ከሮማውያን ሥልጣኔ ወዲህ የፍትሕ ነገር እ ጅግ ሰፊና አስቸጋሪ እየሆነ በመሄዱ ያንድ ወይም የብዙ ሰዎች መልካም ፈቃድ ብቻ ሊያከናውነው አልቻለም ።

ተው በግል በራሱ ስም ሳይሆን ፤ በመንግሥት ሥራ የተቀመጠ ሰው ነው ፤ አብዛኛውን ጊዜ አንድ የፖሊስ ባልደረባ ነው ። ይህ ሰው እራሱ በቀጥታ ሳይነካ ፤ በምን ምክንያት ፤ በየትኛው መብቱ ፤ በማንስ ስም ሊከስ ቻለ? ይህ ሰው ወንጀል ሠራ ተብሎ የተከሰሰውን ሰው የሚሞግተው በሕዝብ ስም ሆኖ ነው ፤ ስሙም ሕግ አስከባሪ ይባላል ።

ሁለቱ ሰዎች በወሰን በተጣሉ ጊዜ መሬቱ የዚያም ይሁን የዚህ የራሳቸው ጉዳይ ነውና ሕዝብን የሚያገባው ነገር የለም ። ግን ጥፋተኛው ነጂና አሸባሪው ሰው በሕዝብ ላይ ጉዳት ስላደረሱ ወይም ሊያደርሱ ስለሚችሉ ፤ ሕዝብ በጉዳዩ የግድ መግባት ይኖርበታል ።

ስለዚህ ቀድሞ ለመሬቱ ቍራጭ የተሟገተው ሰው እንዳደረገው ሁሉ ሕዝብ ፤ ወንጀለኛውን በዳኛ ከሰሰው ፤ ተከታተለው ። በተለምዶ አነጋገር ፤ ዳኝነት ወንጀለኛውን ተከታተለው የሚለው አነጋገር ግን ስሕተት ነው ። በዘመናዊ ሕግ መሠረት ፤ ዳኝነት ማንንም አይከስም የሚከታተልና የሚከስ በሕዝብ ፤ ስም ሆኖ ፤ መንግሥት ነው ። በመሠረቱ ፤ መንግሥት ተሟጋችና ዳኛ ለመሆን አይችልም ፤ በዳኛው ፊት ከሳሹ መንግሥትና ተከሳሹ ወንጀለኛ እኩል ናቸው ።

በሕገ መንግሥቱ ዳኝነት ከመንግሥት የተለየና በሕጉ መሠረት ብቻ የሚሠራ ሥልጣን እንዲሆን የተወሰነው ስለዚህ ነው ።



ሕጐች ፤ በፍትሐ ብሔርም ሆነ በወንጀል ነገር ፍርድ ቤቱና ዳኞች በተጻፉ ሕጐች መሠረት ነው እንጂ በየጊዜው እንደመሰላቸው ሊፈርዱ አይችሉም ።

ዛሬ በኢትዮጵያ ፤ የፍትሐ ብርሔና የወንጀለኛ መቅጫ ሕጐች በዘመናዊ አገሮች ሥርዓትና መልክ ተዘጋጅተው ይሠራባቸዋል ።

በዳኝነት ሥልጣን ላይ ያሉ ሰዎች ፤ የአገረሰቡ ፤ ክብር ፤ ንብረትና ፤ ሕይወት በእጃቸው ስለሆነ ፤ ከማንኛቸውም አመራር ነጻ መሆን አለባቸው ሲል ሕገ መንግሥቱ ወስኗል ።

ስለዚህ ዳኞችን መሾምና መሻር ፤ ተግባራቸውን በትክክል እንዲፈጽሙ አስፈላጊውን ዋስትና መስጠት ለንጉሠ ነገሥቱ ብቻ በተለይ የተሰጠ ሥልጣን ነው ።

## ም ዕ ራ ፍ 3

# የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ግዛት አከፋፈል

በኢትዮጵያ አስተዳደር ፤ በአገር ግዛት ሚኒስትር አማካይነት ሲከናወን ፤ አገሪቱ በ13 ጠቅላይ ግዛቶች ተከፍላለች ፤ አስራ አራተኛ ኤርትራ ከ1945 ጀምሮ ፤ በፌዴሬሺን ከኢትዮጵያ ተቀላቅላለች ፤

ጠቅላይ ግዛቶች በአውራጃ ፣ አውራጆች በወረዳ ፣ ወረዶች በም/ ወረዳ ተከፍለዋል ፤ ጠቅላይ ግዛቶችን የሚያስተዳድር ከንጉሠ ነገሥቱ የተሾመ ፣ ማዕረጉ ከሚኒስትር ጋር ተመዛዛኝ የሆነ ጠቅላይ ገዥ ነው ፤

ጠቅላይ ገዥው ለጠቅላይ ግዛቱ የንጉሠ ነገሥቱ እንደራሴ ነው ፤ እንዲሁም ፣ በጠቅላይ ግዛቱ ውስጥ የሚኒስቴሮቹ ወኪል በመሆን ፣ በዚያ የሚገኙትን የሚኒስቴሩን ቅርንጫፎች በበላይነት ይቆጣጠራል ።

የአውራጃ ፣ የወረዳ ፣ የም/ ወረዳ ገዥዎችም የሚሾሙ ከንጉሠ ነገሥቱ ነው ።

ነገር ግን ከም/ ወረዳ እስከ ጠቅላይ ግዛት ድረስ ፣ ዋናው ሰፍራ ከተማ ስለሆነ ፤ በሚከተለው ምዕራፍ ስለከተሞችና ስለማዘጋጃ ቤቶች በተለይ እንገልጻለን ።

## ም ዕ ራ ፍ 4

# ከተሞችና ማዘጋጃ ቤቶች

በኢትዮጵያ ብዙ ትልቅም ትንሽም ከተሞች አሉ ፣ ነገር ግን እንደየአቅማቸው ማዘጋጃ ቤት ሊኖራቸው ይገባል፤

አንድ ከተማ ፣ በራሳቸው ለመተዳደርና የውስጥ ጉዳያቸውን እራሳቸው እንዲመሩ የተወሰነ መብት ያላቸው ሰዎች በአንድነት የሚኖሩበት ስፍራ ነው ፤



**ማዘጋጃ ቤት ፤**

ማዘጋጃ ቤት ያንድ ከተማ ሰዎች ከተማውን የሚያስተዳድሩበት አቅዋም ነው ፤ ባጀቱንም የሚወስንለት የከተማው ሕዝብ ነው ፤ በማሕበር የሚኖሩም ሰዎች ፤ የተወሰኑ ገቢዎችና ፤ የተወሰኑ ወጭዎች ስላሉዋቸው ሁለቱ የተመዛዘኑ እንዲሆኑ በተቻለ መጠን መድከም አለባቸው ። ስለዚህ የማዘጋጃ ቤቱ ባጀት ፣ በከተማው ሕዝብ ይወሰናል ፤ አብዛኛው ገንዘብ እራሳቸው ከሚከፍሉት የማዘጋጃ ቤት ቀረጥ የተገኘ ስለሆነ ለነሱ ጥቅም ፣ ማለትም ፤ ለከተማው ሕንጻዎች ፣ ለመንገዶች ፣ ለውሃ ሥራና ይህን ለመሳሰለው መውጣት አለበትና ፤ አወጣጡን መቆጣጠር መብታቸው ነው ። ነገር ግን ፤ የከተማው ሕዝብ ሁሉ በጉባዔ ተቀምጦ በጉዳዩ ለመከራከር ስለማይችል ፤ የመቆጣጠርና የማስተዳደር መብታቸውን ፣ ቍጥራቸው ለተወሰነ ሰዎች ወክለው ይሰጣሉ ፤ ማዘጋጃ ቤቱ በከተማው ውስጥ አንድ ድርጅት ያለ ሕንጻ ይይዛል ፤

በውስጡም ዘወትር ፣ ብዙ ሰዎች ሊሰበሰቡና ሊመካከሩ የሚችሉበት ፣ አንድ ሰፊ አዳራሽ ይኖረዋል ፤ የማዘጋጃ ቤት ምክር ቤት ነው ።

የማዘጋጃ ቤት አማካሪዎች ፤ የማዘጋጃ ቤት አማካሪዎች ፣ ብዛታቸው እንደ ከተማው ስፋትና እንደ ሕዝቡ ፣ መጠን ፤ በተወሰነው ደንብ መሠረት ፣ የከተማው ሕዝብ የሚመርጣቸው ሰዎች ናቸው ፤ እነርሱም በደንበኛ ጉባዔ ፤ አስፈላጊም ሲሆን በልዩ ጉባዔ እየተሰበሰቡ ፤ የከተማውን ጉዳይ ፣ ያጠናሉ ፤ በተለይም ባጀቱን ይወስናሉ ።

በሕገ መንግሥቱ መሠረት ፣ ለከንቲባነት የሚገቡ የሶስት ሰዎች ስም መርጠው ፤ ለንጉሠ ነገሥቱ ያቀርቡና ንጉሠ ነገሥቱ ከሶስት አንዱን ይሾመዋል ።

የቀሩት ምክትል ከንቲባዎች ይሆኑና በተለይም ከንቲባው በሌለበት ጊዜ ፣ የሱን ሥራ ፣ ሊሠሩ ይችላሉ ።

የከንቲባው ተግባሮች ፤ የማዘጋጃ ቤት አማካሪዎች ፣ ተሰብስበው በቀረቡ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ይሰጣሉ ፤ የሚያስፈጽመው ግን የምክር ቤቱ ፕሬዚዳንት የሆነው ፣ ከንቲባው ነው ።

ከዚህም በቀር ፓርላሜንት የሚያወጣቸው ሕጎች ፤ መንግሥት የሰጣቸው ትዛዞች ፤ በኢትዮጵያ ከተሞች ሁሉ መፈጸም ስላለባቸው ፤ ለሚያስተዳድረው ከተማ ሕዝብ ማስታወቅና ውሳኔው እንዲፈጸም መጠባበቅ የከንቲባው ተግባር ነው ። ለዚህ ሥራ እንዲመቸው ፣ መንግሥት የወጡትን ሕጎችና የመንግሥት ማስታወቂያዎች በየጊዜው ይልክለታልና እያንዳንዱ የከተማው ሕዝብ እንዲያውቀው ግዴታ ስለሆነ ያስታውቃል ፣ ያስፈጽማልም ።

በማዘጋጃ ቤቱ የሕዝባዊ ሁኔታ መዝገብ እንዲያዝ ያደርጋል ፤

<u>የማዘጋጃ ቤቱ ጽ/ቤትና የገንዘብ አሶተዳደር</u>

ከተማው ትንሽም ይሁን አንድ ጽ/ቤት እንዲኖረው ግዴታ ነው ። በትልልቅ ከተሞች ከፍ ያለ ሕንጻና ሰፊ አስተዳደር አለው ፤



ማዘጋጃ ቤቱ አንድ ባጀት እንዳለው ባለፉት መስመሮች ጠቅሰናል ፤ ማዘጋጃ ቤቱ ፣ ቀረጥን የመሳሰሉ ገቢዎች አሉት ፤ ለመንገዶች ጥበቃ ፣ ለተማሪ ቤቶች ፣ ለደሞዝ ፣ የሚያደርጋቸው ወጭዎች አሉ ፤ እንደ ከተማው መጠን የሂሳብ መዝገቦች የሚይዙ ሠራተኞች ይኖሩታል ።

## ሕዝባዊ ሁኔታ

ሕዝባዊ ሁኔታን የሚከታተለው ክፍል ፣ የያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ፤ ሕይወትና ዋና ዋና ጉዳዮች ይይዛል ፤ ባንድ መሥሪያ ቤት በምንቀጠርበት ጊዜ ፣ ስም ፣ ያባት ስም ፣ እድሜና ይህን የመሳሰሉትን ነገሮች እንጠየቃለን ፤ በቃላችንም ስለምናውቃቸው ለመናገር እንችላለን ፤ እነዚህ ሁሉ ነገሮች ግን ፣ በኛ ወይም በወላጆቻችን አስተዋሽነት ብቻ መያዝ የለባቸውም ፤ ባንድ ደንበኛ ሰፍራ ላይ እንዲመዘገቡ ያስፈልጋል ።

ያንድ ኢትዮጵያዊ የልደት ፣ የጋብቻ ፣ የሞት ፣ ሰነዶች ፣ ሕዝባዊ ሁኔታው ይባላሉ ፤ እነዚህ ሕዝባዊ ሁኔታን የሚገልጹ ሰነዶች በማያሻማ አኳኋን ተሞልተው እንዲገኙ፣ አስፈላጊ ነው ። እያንዳንዱን ሰው በትክክል ለማወቅ ይጠቅማሉ ። በሕዝባዊና ባስተዳደር ኑሮ በሚፈጸሙ ነገሮች ላይ ሁሉ ትክክለኛነትን ያስከትላሉ ።

የሕዝባዊ ሁኔታ አመዘጋገብ ሥራ በመላው ኢትዮጵያ አልተስፋፋም ፣ ቢሆንም ባንዳንዱ ከተሞች ተጀምረዋልና

ባለመብቃታቸው ምክንያት ብዙዎቹ ልጆች ያለ ትምሕ ርት ይቀራሉ ።

ሕግ መሠረታዊ ትምሕርት መማር ግዴታ ነው ሲል ፥ ልጆቹ ተማሪ ቤት መሄድ አለባቸው ማለቱ አይደለም ። ግ ዴታ መማሩ ብቻ ነውና ሕጉ እዚህ ላይ የፈለገው ፤ ማንኛ ውም ሕጻን መሠረታዊ ትምሕርት ለመማር በሚፈቀድ ለት እድሜ ፥ መማር እንጂ ከትምሕርት በቀር ቋሚ ሥራ መያዝና ተቀጥሮ መሥራት የለበትም ሲል ነው ፤ ስለዚህ ያንድ መንደር ወይም ወረዳ ሰዎች ተሰብስበው ፤ አዋጥ ተው ተማሪ ቤት ፥ በመሥራት ወይም አንድ መምሕር ለ ብዙ ቤት ሰብ ልጆች በመቅጠር ልጆቻቸው መሠረታዊ ት ምሕርት እንዲያገኙ ለማድረግ ይችላሉ ። ተማሪ ቤት አ ጣሁ ብሎ ልጅን አለማስተማር ታላቅ በደል ነው ።

## ተራድኦ በከተማ ውስጥ

የከተማው ሕዝብና ማዘጋጃ ቤቱ ፥ በተፈጥሮ ጉድለት ወይም በአደጋ ምክንያት ስንኩል የሆኑትን ሁሉ ፥ ችግራቸ ውን ማቃለል ዓይነተኛ ተግባራቸው ነው ።

እርዳታ ፤ ሰው ሁሉ በደስታና በምቾት ላይ አይገኝም ። በልዩ ልዩ ምክንያቶች ፤ ለምሳሌ በበሽታ ፤ በቤተሰብ አባት መሞት ፥ በሥራ መፍታትና ይህን በመሳሰለ ነገር ፥ አቅም በማጣት ፥ ፍጹምና አሳዛኝ በሆነ ችግር ይጠመዳሉ ። እያን



ዳንዳችን ፥ እንደየ አቅማችን ፥ እንደዚህ ያሉትን ሰዎች ፥ መርዳት የማይታለፍ ግዴታችን ነው ። ነገር ግን የያንዳንዳ ችን አቅም አነስተኛ ስለሆነ ፤ እርዳታው ጥቅም ሊሰጥ የሚ ችለው በማሕበር ቢደራጅ ነው ።

በጠቅላላው እላይ በተባለው ሁኔታ የሚገኙ ሰዎች ፥ እንዲረዱ በመንግሥት በኩል የተቋቋሙ ስፊ ድርጅቶች አሉ ፤ ቢሆንም የከተማው ሕዝብ በበኩሉ ደግሞ የተራድኦ ማሕበሮች ማቋቋምና መረዳዳት አለበት ።

ለምሳሌ የበጎ አድራጎት ጽ/ቤት ተቋቁሞ ፥ ከልዩ ልዩ ሰዎች የሚሰጠውን ገንዘብ ፥ ከማዘጋጃ ቤቱ የሚያገ ኘውን እርዳታና ሌሎችም ስጦታዎች እያደላደሉ ፤ ለተቸ ገሩ ሰዎችና ፥ ቤተሰቦች በየመጠኑ ማከፋፈል ይችላል ።

ሆስፒታሎችና ፥ የጡረታ ቤቶች ፤ ማዘጋጃ ቤቱ ሆስፒ ታሎችና የጡረታ ቤቶች ማቋቋም አለበት በመሠረቱ ሁለ ቱም ፥ ለችግረኞችና ፥ ለደካሞች የተዘጋጁ ስለሆነ ፥ እርዳ ታቸውን በነጻ መስጠት አለባቸው ፤ ሆስፒታሎቹ በሽተኞ ቹን እያስታመሙ ድነው እስኪወጡ ፥ ድረስ ብቻ ይረዷቸ ዋል ፤

የጡረታ ቤት ግን ደካሞችና ሽማግሌዎች ፥ ቀሪውን እድሜያቸውን ከረሃብ ፥ ከችግርና ከጉዳት ተጠግተው የሚ ያሳልፉበት ስፍራ ነው ።

የበጎ አድራጎት ጽ/ቤት ፥ ሆስፒታሎች ፥ የጡረታ ቤቶች በጠቅላላው ፥ ማሕበራዊ መረዳጃ ይባላሉ ።

# በከተማ ውስጥ ሕዝባዊ ማኅበሮች ።

የተቋቋመውን ሕግ አይጣሱ እንጂ ፣ የሚፈቅዱትን ዓይነት ሥራ ለማከናወን ፣ ብዙዎች ሰዎች በሚመስላቸው መንገድ ፣ በማሕበር መቋቋም ይችላሉ ።

እስካሁን ድረስ ያጠናነው በሕግ የተወሰኑትን ደንበኛ አቋሞች ፣ ሠራተኞችና ፣ ድርጅቶች ነው ። የኢትዮጵያ ሕገ መንግሥት ፣ አገረሰቦች ፣ በሚመስላቸው መንገድ በማሕበር እንዲቋቋሙ ፣ ይፈቅዳል ። ነገር ግን ፣ የማሕበሩ ዓላማ ግልጽ እንዲሆንና ፣ አድራጐቱም ሁሉ ፣ የሕብረሰብን ጥቅም የማይነካ እንዲሆን ግዴታ ነው ። ለምሳሌ ያህል ጥቂቶች እንጠቅሳለን ።

<u>መንፈሳዊ ሕብረቶች ፤</u> የኢትዮጵያ መደበኛ ሃይማኖት ፣ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን መሆኗ በሕገ መንግሥቱ ሲነገር ፣ በሌላ ሃይማኖት ማመን ወይም አለማመን ለሕዝቡ መብት ሆኖ ተሰጥቷል ፤ ስለዚህ ባንድ ከተማ ውስጥ ኦርቶዶክሳዊ ፣ ካቶሊካዊ ፣ የፕሮቴስታንት (ወንጌላዊ) ቤተ ክርስቲያኖች ፣ እስላማዊ ፣ መስጊድ ፣ እሥራኤላዊ ፣ ሲናጐግ ፣ ይታያሉ ፤ በነዚህ ልዩ ልዩ ሃይማኖቶች የሚያምኑ ሁሉ ፣ በየቤተ ጸሎታቸው እየተሰበሰቡ ፣ የሃይማኖታቸውን ሥርዓት በፍጹም ነጻነት ለማክበር ይችላሉ ።

<u>ፖለቲካዊ ሕብረቶች ፤</u> ፖለቲካዊ ሕብረቶች በኢትዮጵያ አልተቋቋሙም ። ነገር ግን ማንኛውም ሰው ፖለቲካ



ዊ አስተያየቱን ፣ ሕግን ሳይተላለፍ በንግግርም በጋዜጣም ለመስጠት ሙሉ መብት አግኝቷል ።

<u>የሠራተኞች ማሕበር ፤</u> ሕብረት ኃይል ነው የተባለ እምነት አለ ፤ አንድ ዓይነት ሥራ የሚሠሩ ግለ ሰቦች ፣ መጠበቅ የሚገባቸው የጋራ ጥቅሞች አሏቸው ፤ ለምሳሌ ፣ የሥራ ምቾታቸውን ገቢያቸውን (ደሞዝ ፣ አበል ፣ ትርፍ ፣ የድካም ፣ ዋጋ ፣ ) ለማሻሻል ፣ እንዲሁም ከነሱ መካከል በልዩ ልዩ ምክንያት የራሳቸውንና የቤተ ሰባቸውን ጥቅም ለመጠበቅ ያልተመቻቸውን ለመርዳት ፣ ይጥራሉ ፤ ስለዚህ የሠራተኞች ማሕበር ማቋቋም ጠቃሚ ነው ፤ እነዚህ ማሕበሮች በእንግሊዘኛ ሲንዴኬት ይባላሉ ።

ሠራተኞቹ ራሳቸው ፣ ባለፋብሪካዎችም ፣ ሐኪሞች ፣ መሐንዲሶች ፣ ነጋዴዎች ፣ ጸሐፊዎች ፣ በየበኩላቸው በማሕበር ሊቋቋሙ ይችላሉ ፤

እነዚህ ድርጅቶች የሚሰጡት ጥቅም በጣም ከፍ ያለ ነው ፤ ለምሳሌ የግንበኞች ፣ ማሕበር የተቋቋመ እንደሆነ ፤

ሀ) ማንኛውም ግንበኛ ካንድ ከተወሰነ ደሞዝ በታች እንዳይቀጠር በመስማማት ፤ ቤት ሠሪና ፣ ባለ ሃብት ፣ በአነስተኛ ደሞዝ እንዳያጉላላቸው ለማድረግ ይችላሉ ፣ የሥራውን ዋጋ በማስቀረት ቀጣሪ እንዳያጉላላውም በሕግ ፊት ተከራካሪ ሆኖ ይቆምለታል ።

ለ) ከሚያገኙት ገንዘብ ላይ የተወሰነ መቶኛ እያዋጡ በማኅበሩ ሣጥን በማኖር ፣ ሥራ በፈቱ ጊዜ ፣ በታመሙ ጊዜ

ወይም ሌላ ጉዳት በደረሰባቸው ጊዜ ፣ የሚተማመኑበት እርዳታ ያደራጃሉ ፤

መ) የግንብን ሥራ ጥበብ የማሻሻል እርምጃ ለመውሰድ ያመቻቸዋል ፤ በመሠረቱ ይህን የመሳሰሉ ብዙ ጥቅሞች ሊያገኙበት ይችላሉ ። ደግሞ በትልልቆች ከተሞች የሚገኙ የጢም ላጭዎች ሱቆች የጥቂት ሰዎች ንብረት ስለሆኑ ፣ ጠጉር አስተካካዮች ቀጥረው ይሠራሉ ፤ የሚከፍሏቸውም ጥቂቶች ባለንብረቶች ተስማምተው የወሰኑትን ፣ ከመቶ ይህን ያህል ብለው ነው ፤ ከተቀጣሪዎቹ አንዱ ይህን ዋጋ አልቀበልም ቢል ፣ ቀጣሪው ከሥራ ያሰናብተዋል ፤ አንዱ ያሰናበተውንም ሌላው እንዳይቀጥር በቀጣሪዎች መካከል ልዩ ስምምነት ስላለ ፣ ይህ ሰው ወይም ሥራ ፈት መሆን ፣ ወይም የሠጡትን አበል ተቀብሎ መሥራት አለበት ፤ ነገር ግን ተቀጣሪዎቹ ማሕበር ቢያበጁና ጥቅምና መብታቸው በሱ አማካይነት እንዲጠበቅ ቢያደርጉ ተገቢ ደሞዝ ለማግኘትና ሰባዓዊ ያልሆነ በደል እንዳይፈጸምባቸው ለመከላከል በቻሉ ነበር ፤

በሥነ ፡ ጥበብ ረገድ ደግሞ ፣ ሙዚቀኞች ፣ ደራሲዎች እንደዚሁ በማሕበር እየተቋቋሙ ሥራቸውን ለማስፋፋት ችለዋል ፤

<u>ስፖርታዊ ማህበሮች ፤</u> በግለሰብ ሊደረጉ የሚችሉ ብዙ እስፖርቶች አሉ ፣ አብዛኞቹ ግን በብዙ ሰዎች መካከል የሚደረጉ ናቸው ፤ ስለዚህ የነዚህ ስፖርት አፍቃሪዎች፣ በግድ በማሕበር መቋቋም አለባቸው ። ለምሳሌ ቴኒስ ፣ ፉትቦል ወይም ቦክስ የሚያዘወትሩ ሰዎች መጫዋቻቸውን ስፍራና መለማመጃውን ቤት እያንዳንዳቸው ፣ ሊያሠሩ ያስቸግራልና ፣ ማሕበርተኞቹ ለሆኑት ሁሉ አስፈላጊውን ስፍራ በመግዛት ወይም በመከራየት በሚያቀርብላቸው ባንድ ማሕበር መመዝገብ ይኖርባቸዋል ። ይህም ማሕበር ስፖርታዊ ማሕበር ይባላል ። የነዚህ ማሕበሮች መቋቋም ለማሕበራዊ ኑሮ የሚሰጠው ጥቅም ፣ ከፍ ያለ ግምት አለው ፤ በተለይም በዛሬው የሥልጣኔ ዘመን ፤ ሰው በተፈጥሮ የተሰጠውን አካሉን ከድካም ለማዳን በቴክኒክና ፣ በመኪና አገልግሎት እየተጠቀመ ፣ ጣትን እንኳን ሳያንቀሳቅስ ፣ ለመኖር የሚችልበትን መንገድ ይፈልጋል ። የሰው አካልም ፣ ሲፈጠር የተመደበለትን ፣ ሥራ ሲተው ፣ መቀጨጨና ፣ መድከሙ ፣ የተመረመረና የተረጋገጠ ስለሆነ ፣ በሥራ ምክንያት ፣ ያገኘው የነበረውን አሁን ግን የተከለከለውን ቅስቃሴ ፣ በሌላ ዘዴ ለማግኘት እንዲችል ማድረግ ግዴታ ነው ደግሞም ሰው ዕውቀቱን እያራቀቀ በምድር ላይ ብቻ ሳይሆን ከምድርም ውጭ ያሉትን ኃይሎች በቴክኒኩ ሊገዛቸውና ሊጠቀምባቸው በብዙ ስለሚደክም ፣ ከፍ ያለ አእምሮ ያስፈልገዋል ። ይህም አእምሮ ሊኖር የሚችለው በጤናማና በብርቱ አካል ውስጥ ብቻ መሆኑ ከጥንት ጀምሮ የተነገረና የታመነ ስለሆነ ፣ አካሉን ችላ ሊለውና ለነፍሳቸው ያደሩ ሰዎች ያደርጉት እንደነበረ ሁሉ፣ሊያጐሳቅለው አይችልም።

ዳግመኛም እስፖርት የሰውን አካላዊ ጤንነትና ጥንካሬ በመጠበቁ ፣ ለአገሪቱና ለሕብረ ሰብ ከፍ ያለ አገልግሎት ሊያቀዳጁ የሚችሉ ሰዎች ያተርፋል ። በስፖርት ውድ

ድሮችም ሰው በመወዳደር ድፍረትን ፥ መሸነፍን በሰላም በመቀበል ፥ ትግስትንና እውነተኛነትን ፥ ማሕበረተኛ መሆንና ሕጉንም በማክበር ፥ ስልጡንነትንና የሕብረት መንፈስን ፥ እነዚህን የመሳሰሉ ሞራላዊ ባሕርዮችን ስለሚሳተፍ ፤ ስፖርት የአካል ብቻ ሳይሆን የመንፈስም መድህን ነው ። ስለዚህ ያንድ ከተማ ሕዝብ ፥ ልጆቹ ፥ ወንድሞቹ ፥ እሱ ራሱ ፥ በስፖርትና በሚያስከትለውም ጸጋ ለመጠቀምና ለሕብረሰብ ተገቢ ሰዎች በማግኘት ፥ ማሕበሩን ፥ ራሱን ለማጠንከር ፥ በከተማው ውስጥ ፥ የስፖርት ማሕበሮች ማቋቋም ፥ በገንዘብ መርዳትና ስታዲዮሞች መሥራት የማይዘነጋ ተግባሩ ነው ።

## ስለማኅበሮች መቋቋም ከመንግሥት የሚጠየቀው ።

ማሕበር ማቋቋም በሕግ ያልተከለከለ መሆኑን ባለፉት መስመሮች ፥ ገልጸናል ። መንግሥት እንዲያመለክቱ ብቻ ይጠይቃል ። በማመልከቻው ላይ የማሕበሩን መጠሪያ ትክክለኛ ፥ ስም ፥ ዓላማውንና መሥሪያ ቤቱ የሚገኝበትን ሥፍራ ፥ መዘርዘር ያስፈልጋል ፤ ይህ ማመልከቻ ፤ ባዲስ አበባ ባገር ግዛት ሚኒስቴር ፥ በሌላ ከተማ ሲሆን ለግዛቱ ጽ/ቤት መድረስ አለበት ። ባለፉት ገጾች ባጭሩ ስለከተማና ስለማዘጋጃ ቤቱ አስተዳደር ጽፈናል ፥ ባጭሩም ስንመለከተው ፤ ከተማ በከተማ ሕዝብ ወኪሎች መመራቱን ፥ በውስጡ የሚፈጽማቸውን ዋና ዋና ተግባሮች ዘርዝረናል ፤



በተረፈ የከተማው ሕዝብ ፤ የተወለደበትን ወይም የሚኖርበትን ከተማ መውደድ ይገባዋል ። ይህ የራስ ከተማ ፍቅር ያገርን ፍቅር በምንም አኳኋን አይቀንሰውም ።

እንዲያውም ይህ ከሥር የተጀመረ ፍቅር ለታላቁ ለአገር ፍቅር በበለጠ አኳኋን ፤ ትምሕርትና መዘጋጃ ይሆናል።

ስለዚህ የከተማው ሕዝብ እያንዳንዱ ውበቷን መጠበቅና እየተሻሻለች እንድትሄድ ከተማውን መርዳት አይነተኛ ተግባሩ ነው ።

## ምዕራፍ 5 ፤

## ሚኒስቴሮች ።

ባለፉት ገጾች የኢትዮጵያን አስተዳደር አከፋፈል ፥ የከተሞችን አኗኗርና የማዘጋጃ ቤቶችን ተግባሮች ገልጸናል ፥ ነገር ግን ጠቅላይ ግዛቶችና በውስጣቸው ያሉት መሥሪያ ቤቶች ፥ ተጠቃለው ፥ በዋናው ከተማ በአዲስ አበባ ላይ በሚገኙ ሚኒስቴሮች ይመራሉ ።

ለምሳሌ የወረዳ ገዥያችሁ አንድ አዋጅ ቢያሰማችሁ ፥ ይህ አዋጅ ፥ በመጀመሪያ ፥ ከአገር ግዛት ሚኒስቴሩ ፥ ለጠቅላይ ግዛቱ ፥ ከጠቅላይ ግዛቱ ፥ ለአውራጃው ለወረዳው ፥ ሲተላለፍ የመጣ ነው እንጂ ፥ በቀጥታ ከወረዳው የፈለቀ አይደለም ።

ሚኒስቴር ማለት ምን ማለት ነው ? ፣ ሚኒስቴሮች የኢትዮጵያ ያንድ ክፍል ጉዳይ ሳይሆን ፤ መላ አገሩን የሚመለከቱት ጉዳዮች ሁሉ የሚፈጸሙባቸው አቋሞች ናቸው ።

የሚኒስቴሮች ዋና መሥሪያ ቤቶች ሁሉ የሚገኙት አዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ነው ፤ ነገር ግን በየጠቅላይ ግዛቱ የያንዳንዱ ሚኒስቴር አንድ ድሬክሲዮን ይገኛል ።

የሚኒስቴሮች ሕንጻዎች ታላላቅና በጥሩ አኳኋን የተሠሩ ናቸው፤በተለይም የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ብዙ የውጭ እንግዶች ስለሚቀበል ፣ ጥሩ፣ ጥሩ፣ ሳሎኖች ያስፈልጉታል።

ሚኒስትር ፤ ከላቲን ፣ ሚኒስተር ፣ ማለት አገልጋይ ከሚለው ቃል የፈለቀ ስም ነው ፤ ስለዚህ የመንግሥቱ አገልጋይ ነው ። ብዙዎቹ የሚኒስትር ሥራ ማዘዝ ብቻ እየመሰላቸው እንዴት አገልጋይ ይባላል የሚሉ አሉ ፤ ነገር ግን ፣ ትዕዛዝም ቢሰጥ በመንግሥት ስምና ፣ ለሕዝብ አገልግሎቱት ነው እንጂ በራሱ ስምና ለራሱ አገልግሎት አይደለም ፤ በዚህም የተነሳ ፣ የሕዝብ እንደራሴ የሆኑት የፓርላሜንት አባሎች ሥራውን ይቆጣጠሩታል ።

በዴሞክራቲክ አገሮች ለሚኒስትር ሕጋዊና ሞራላዊ ሥልጣኑን የሚሰጠው ይህ ሁኔታ ነው ።

ልዩ ልዩ ከፍያለ የሥራ ክፍል ባለባቸው ሚኒስቴሮች፣እያንዳንዱን ክፍል የሚመሩ፣ምክትል ሚኒስቴሮች አሏቸው።

ሚኒስትሮች እንደሚታሰበው ሁሉ የሚኒስቴራቸውን ሥራ በተለይ የተማሩ መሆን የለባቸውም ፣ ለምሳሌ ፣ የጤና ጥበቃ ሚኒስትር በግዴታ ሐኪም መሆን የለበትም ፣ የሥራ ሚኒስትር በግዴታ መሐንዲስ እንዲሆን አያስፈልግም ፣ የሚኒስትሮች ተግባር ማስተዳደርና መምራት ስለሆነ ባንድ ዓይነት የትምሕርት ቅርንጫፍ የበቃ ብስለት ካላቸው ማንኛውንም ሚኒስቴር ለመምራት ይችላሉ ።



ሚኒስትሩ በቀጥታ ራሱ የሚቆጣጠረው ልዩ ጽሕፈት ቤት እንዲኖረው ያስፈልጋል ።

ባንድ ሚኒስቴር ውስጥ ልዩ ልዩ ድሬክሲዮኖችና ፣ የጽሕፈቱን ሥራ በጠቅላላ የሚያከናውን ፤ አንድ ዋና ጽሕፈት ቤት አለ ።

የሚኒስትሩ ትዕዛዝ በትክክል መፈጸማቸውን ፣ በስፍራው ላይ ሆኖ ለመመርመርና ፣ የምርመራውንም ፍሬና ፣ ያስተዳደሩን ሁኔታ ለሚኒስትሩ ለመግለጽ የተቋቋመ ፤ አንድ የኢንስፔክተሮች ጽ/ቤት አለ ።

ተግባራቸውም በየጠቅላይ ግዛቱ እየተዘዋወሩ የሚኒስቴሩን መ/ቤቶችና ሠራተኞቹን በመቆጣጠር ሥራው በምን አኳኋን እንደሚመራ ፣ የተገኘውን ጉድለት ፣ ለወደፊቱ ማድረግ የሚገባውን መሻሻል ሁሉ መግለጽ ነው ።

## የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች አስተዳደርና ተግባር ።

መንግሥት ፣ የሕዝቡን ጠቅላላ ጥቅሞች ለመጠበቅ ፣ ከአገረሰቡ በተሰጠው አደራ መሠረት የአገሪቱን መሬት አለ

— በዘመናዊ አገር ውስጥ ፤ አቅም ያላቸውና የተመቻቸው ፣ ያልታደሉትንና ደካማዎችን ፣ መርዳት አለባቸው ፣ ዝግጅቱ የመንግሥት ሥራ ነውና ፣ ተራድኦና ሕብረ ሰብዓዊ ሥራ መፈጸም የጡረታ ሚኒስቴር ተግባር ነው ።

— ላገሪቱ የሚያስፈልገውን የገንዘብ ወጭ አገረ ሰቡ በማዋጣት መቻል አለበትና ፤ ይህን ገንዘብ መሰብሰብና ማከፋፈል የመንግሥት ፋንታ ነው ፣ የገንዘብ ሚኒስቴር ተግባር ነው ።

— ምንም እንኳን እያንዳንዱ ሰው የራሱን ጤና ቢጠብቅ ፤ ማኅበራዊ ኑሮ የጋራ ጤና አጠባበቅ ድርጅት ይጠይቃልና ፣ የጋራ ጤና አጠባበቅ ሥራ ካልተፈጸመም የያንዳንዱን ሰው ጤና መጠበቅ ፍሬ አይሰጥምና ፣ መንግሥት ይህን ሥራ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ያስፈጽመዋል ።

— በተረፈ የእርሻ ፣ የንግድ ፣ የኢንዱስትሪና ፣ የመሳሰለውም ሁሉ ሥራዎች ፣ አብዛኛውን ጊዜ በግለሰብ አማካይነት ቢከናወኑም ፤ ከጠቅላላው ያገሩ ጥቅም ጋራ የተያያዙ ናቸው ።

የመመላለሻና የመገናኛ ሥራዎችም መንግሥታዊ ድርጅቶች ናቸው ። የነዚህ ሥራ አመራር በጠቅላላው የአካላዊ ኑሮ ድርጅት ይባላል ። አካላዊ ኑሮ የተባሉበትም አገረ ሰቡ ለሕይወቱና ለኑሮው አስፈላጊ የሆኑትን ፣ ምግብ ፣ ልብስ ፣ መመላለሻና መገናኛ የሚያቀርቡለት ስለሆን ነው ። ከዚህ በላይ የተዘረዘረው የሚኒስቴሮቹን የደረጃ አያያዝ ሳይሆን ፣ የመንግሥቱ ሥራ መዘርዘሪያ ልንለው ይገባል ።



በዚህ አኳኋን የመንግሥቱን ሥራ እሁለት ላይ ልንከፍለው እንችላለን ፤

1 ሞራላዊ ተግባር ፣ አገር መከላከያን ፣ ዳኝነትን ፣ ጸጥታን ፣ ትምህርትን ፤ ጡረታን ፣ መተዳደሪያ ገንዘብን ፣ ጤና ጥበቃን ፣ ይይዛል ፤

2 አካላዊ ድርጅት ፣ እርሻን ፣ ንግድን ፣ ኢንዱስትሪን ፣ መመላለሻን ፣ መገናኛን ይይዛል ፤ ከዚህ ቀጥሎ መንግሥት እነዚህን ሥራዎች እንደምን እንደሚያከናውን እንመልከት ፣

## የውጭ ግንኙነት

የመንግሥቱ ፍጹምነት የሚታወቀው ከሌሎች አገሮች ጋር በሚያደርገው ግንኙነት ነው ።

የዲፕሎማሲ ሥራ ጠቃሚነት ፤ ጦርነት ከጥንት አባቶች ጀምሮ የቆየ ነገር ቢሆንም ፣ በስምምነትና በመመካከር ለማስቀረት የሚቻል መሆኑን ሰው ከብዙ ዘመን ጀምሮ አውቆት ተረድቶታል ። ቀጥሎም መንግሥታት በእንደራሴዎቻቸው ፣ አማካይነት ተነጋግረውበት በስምምነት የማይፈጸም ሲሆን ፤ ጦርነት ከመነሳቱ አስቀድሞ ፣ ማስታወቂያ መስጠት ግዴታ ሆነ ። በጦርነትም መካከል ፣ መልክተኛ

ያላንዳች መሣሪያ ጠላት ዘንድ ሄዶ ለመነጋገርና ለሕይወቱም ሳይሰጋ ለመመለስ እንዲችል መብት ነበረው ። የዲፕሎማሲ ሥራ ከዚህ ተያይዞ የመጣና በመንግሥታት መካከል ግንኙነትን ለማጥበቅ ፤ የአገርንም ምድር ለማስከበር የሚጠቅም ፤ ነገር ነው ። ይህ ሥራ የሚከናወነው ፤ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ነው ።

<u>የዲፕሎማሲ መልክተኞች ፤</u> የዲፕሎማሲ መልክተኞች አምባሳደሮችና ቆንሲሎች ናቸው ።

አምባሳደር ፤ በውጭ አገር የመንግሥቱ እንደራሴ ነው ። ባንድ አገርም ካንድ አምባሳደር የበለጠ ሊኖር አይችልም ። የሚኖረውም ፤ በተላከበት አገር ዋና ከተማ ነው ።

ከፍ ያለ ግንኙነት በሌለበት አገር ባለሙሉ ሥልጣን ሚኒስትር ብቻ ማድረግ ይቻላል ።

ቆንሲል ግን ዓይነተኛ ተግባሩ ፤ በውጭ አገር የሚኖሩትን የኢትዮጵያ ተወላጆች የግል ጥቅማቸውን ማስከበር ነው ። ዳግመኛም በማዘጋጃ ቤቶች ምዕራፍ ፤ ላይ እንደገለጽነው ፤ በውጭ አገር የሚወለዱትን ኢትዮጵያውያን ሕዝባዊ ሁኔታ የሚመዘግብ እሱ ነው ። በውጭ አገር የሚጋቡትንም ኢትዮጵያውያን ጋብቻ እንደ ከተማ ከንቲባ ሆኖ ያስፈጽማል ፤ ይመዘግባል ።

ቆንሲሎች የሚቋቋሙት የኢትዮጵያ ተወላጆች በብዙ በሚገኙባቸው ፤ የውጭ አገር ከተሞች ነው ። ለምሳሌ ፤ በጐረቤቶቻችን በጂቡቲና በናይሮቢ ከተሞች ቆንስላዎች አሉን ።



# የመከላከያ ሚኒስቴር ፤

በዛሬ ጊዜ ፤ አገሪቱን የመጠበቅ ተግባር የልዩ ልዩ መሣሪያዎችን ክፍሎች ፤ አጠቃሎ ለያዘ ላንድ ጠቅላላ ድርጅት ተሰጥቷል ።

ስለዚህ የምድር ፤ የአየርና ፤ የባህር ኃይሎች ተጠቃለው በዚህ ሚኒስቴር ስር ፤ ይተዳደራሉ ።

<u>የጦርነት ስንኩሎች ፤</u> በጦር ሜዳ በደረሰባቸው ጉዳት ምክንያት ስንኩል የሆኑ ሰዎች ፤ በመከላከያ ሚኒስቴር አማካይነት ፤ ካሣቸውን ይቀበላሉ ። ይህም የካሣ አከፋፈል ፤ እንደተራድኦና እንደ በጐ አድራጐት አይቆጠርም፤ ምክንያቱም እነዚህ ሰዎች ፤ ጉዳት የደረሰባቸው ፤ መንግሥት ሊያስቀረው ባልቻለ ጦርነት ላይ ገብተው ተግባራቸውን ሲፈጽሙ ስለሆነ ከዚህ ጉዳት ሊያድናቸው ባለመቻሉ ከመንግሥት ካሣ እንጂ ፤ እርዳታ መቀበላቸው አይደለም ። ይህም በሕግ እንዳገኙት እንጂ እንደ ጡረታ አይቆጠርባቸውም ።

በአገራችን የወታደራዊ አገልግሎት ግዴታነት ገና ስላልተቋቋመ ፤ የወታደርነት ሕይወት ያልቀመሱ ብዙ ሰዎች አሉ ፤ ነገር ግን በአገሪቱ ላይ አንድ አደጋ በደረሰ ጊዜ በነጭ ለባሽ ስም እየዘመቱ ሕዝባዊ ግዳጃቸውን ይፈጽማሉ ።

# ጸጥታና ዳኝነት ፤

ኃይለኛ የሆነ የፖሊስ ድርጅት ከሌለ ጸጥታ ባገር ውስጥ ሊኖር ያስቸግራል ። በሰዎች መካከል የሚነሳውንም ሙግት ያለ አድሎና ያለ ስጋት ለመዳኘት የሚችል አቅዋም ከሌለ ፤ ጸጥታና ሰላም ጨርሶ ለመኖር አይችልም ።

ስለ ጸጥታ አጠባበቅና ስለ ዳኝነት ተግባር ፥ በማዘጋጃ ቤቶችና በዳኝነት ሥልጣን ምዕራፍ ዘርዝረናል ።

# ትምህርት ።

ከአርባና ሃምሳ ዓመት ከማይበልጥ ጊዜ በፊት ትምህርት በቤተ ክህነትና በቅዱሳን መጻሕፍት የተወሰነ ነበረና ፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከዘመናዊ ትምህርት ጋር ሳይተዋወቅ ፥ ብዙ ዓመታት ቆይቷል ። ፋሽስት ኢትዮጵያን ከመውረሩ በፊት ፥ አንዳንድ ሚሲዮኖች ፥ እንዲሁም መንግሥታዊ ት/ቤቶች ተቋቁመው የውጭ አገር ትምህርት ለኢትዮጵያ ሕዝብ ስለ ተከፈተለት ፥ ብዙዎች ወጣቶችም ወደ ውጭ አገር እየሔዱ ከፍተኛ ፥ ደረጃ ትምህርት በማግኘታቸው ፥ አገራችን ለዘመናዊ አስተዳደር የሚረዱት የመጀመሪያዎቹን ሰዎች አገኘች ፤

ኢትዮጵያ ነጻነቷን እንደገና ካገኘች በኋላ ግን ፤ መንግሥት ፥ የባጀቱን አብዛኛ ክፍል ለትምህርት በማዋሉ ፤



ዛሬ ሐገራችን የራስዋ ሐኪሞች ፥ የራሷ መሐንዲሶች ፥ የራሷ የሕግ ሰዎች በመጠኑ አሏት ።

ትምህርት የሚመራው ፥ በትምህርት ሚኒስቴር ፥ በንጉሠ ነገሥቱ የበላይ አዛዥነት ነው ።

የአንደኛ ደረጃ ፥ የሁለተኛ ደረጃና የኰሌጅ ትምህርት በቀጥታ በአገራችን ለመስጠት ተችሏል ።

ዩኒቨርሲቲም ባሁኑ ዓመት ተከፈተ ፤ ብዙው ፥ ትምህርት ዛሬ ፥ በእንግሊዝኛና በፈረንሳይኛ ቋንቋ ይሰጣል ፥ ሆኖም የአንደኛ ደረጃ ትምህርት በአማርኛ ቋንቋ ሊሰጥ ተጀምርዋልና የከፍተኛ ደረጃም ትምህርትም ፥ በኛው ቋንቋ የሚሰጥበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም ።

በተረፈ ፥ ወጣቶች ሞያ የሚማሩባቸው ተማሪ ቤቶች ተቋቁመው ፥ ብዙ ተማሪዎች ስለፈለቁ ዛሬ በልዩ ልዩ መ/ቤቶችና በባንክ ፥ በሌላም አቅዋሞች ኢትዮጵያውያኖች ከፍ ያለ የአላፊነት ቦታ በብዛት ይዘው ይገኛሉ ፤ ከነዚህም ተማሪ ቤቶች የንግድን ትምህርት ቤት ፥ ተግባረ እድን፥ ሕንጻ ኰሌጅን ፥ መጥቀስ እንችላለን ፤

እያንዳንዱ ሚኒስቴር ደግሞ ፥ ለራሱ ሥራ የሚያስፈልጉትን ሠራተኞች ለማሠልጠን ፥ ልዩ ልዩ ተማሪ ቤቶች ከፍተዋል ።

ለምሳሌ ፥ የእርሻ ኰሌጅ ፥ ለእርሻ ሚኒስቴር ፤

የአየር ፥ የባህርና ፥ የምድር ጦር አካዳሚዎች ለመከላከያ ሚኒስቴር ፤

ይህን የመሳሰሉ ይገኛሉ ።

የትምህርት ሚኒስቴር ፣ ጤነኛ አእምሮ በጤነኛ አካል የተባለውን ቃል በመከተል ፣ በውስጡ የስፖርትን ድርጅት የሚመራ ሰፊ ክፍል አለው ፣ እንዲሁም የስፖርት ውድድሮችን በተማሪዎች መካከል የሚያዘጋጅ ፣ የተማሪ ቤቶች ስፖርት ማህበር የተባለ አቋም አለው ፤

የኰሌጆችም የስፖርት ማኅበር በዚሁ መልክ ተቋቁሚል ፤

## ልዩ ማስታወሻ ።

በላይኞቹ መስመሮች እንደገለጽኩት ፣ ዘመናዊ ትምህርት አገራችን ከገባ ፣ ብዙ ጊዜው አይደለም ። ስለዚህ ዛሬ አንድ ልጅ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ሲጨርስ ፣ ከወላጅ አባቱና እናቱ በትምህርት ይበልጣል ። ይህ ሁኔታ በቤተሰቦች መካከል ከፍ ያለ ችግርን ፈጥርዋል ፣ ልጅዬው አባትና እናቱ የማያነቡትን በማንበብ የማይጽፉትን በመጻፍ ፣ ከነሱ ይበልጥ ማወቁ ይሰማውና እንምከርህ ፣ ወይም እንዘዝህ ፣ ሲሉት ፣ እናንተ ምን ታውቃላችሁ ማለት አመጣ ፣ አባትና እናትም ፣ ምንም ቢሆን ካንተ ትምሕርት የኛ ከመቆየት የተገኘ ልምድ ይበልጣልና እንዳልህን እደር ሲባባሉ፣ እስከ መለያየት ይደርሳሉ ።

በውጭ አገር ከፍተኛ ደረጃ ተምረው የመጡትም ፣ ባንድ መ/ቤት ሲገቡ ፤ የበላዮቻቸው በትምሕርት ከነሱ



ያነሱ መሆናቸውን ስለሚገምቱ ፣ በምን ምክንያት በደረጃስ ፣ በደሞዝስ ይበልጠኛል ፣ ለምንስ ያዘኛል የማለት ስሜት ያድርባቸዋል ። ያም የቆየ ሹም ፤ ባቀናሁት ቤትና ዘርዝሬ መንጥሬ በማውቀው ሥራ ዛሬ መጥቶ ከኔ ሊበልጥ ነው ወይ በማለት ፤ በሁለቱ ትውልድ መካከል ስምምነት ርቋል ፤

ስለዚህ በኔ አስተያየት ለዚህ መድኃኒቱ ፤

1 ተማሪው ፤ አባትና እናት ያስተማሩት እንደነሱ አላዋቂ ሆኖ እንዳይቀር ፣ እውቀት ሸምቶ በአዲሱ ትውልድ ውስጥ ተገቢውን ስፍራ ተሻምቶ ሊይዝ እንዲችል ፣ በማሰብ ስለሆነ ፣ ባያምንበትም እንኳን ውለታውን ለመመለስና ፣ ለክብራቸው ሲል ፣ ምክራቸውን ቢቀበል አይከፋም ፤

2 አባትና እናትም ፣ የሚመክሩትና የሚያዙት ልጅ ከተማሪ ቤት ፣ የቀሰመው የራሱ አስተያየት ያለው መሆኑን በመገንዘብ ፤ በቆየው ልምዳችን ዓይንህን ጨፍነህ ፣ አስተያየትህን አፍነህ እኛን ብቻ ስማ ማለቱን ቢተው መግባባት ይፈጠራል ፤

3 ከፍተኛ ደረጃ ደርሰው በሥራ ላይ የተቀመጡትም ፤ የበላዮቻቸው ምንም እንኳ በመሠረቱ በትምሕርት ደረጃ ባይደርሱባቸው ፣ እነሱ እንዲማሩና እዚህ እንዲደርሱ ያደረጉ እነሱ መሆናቸውን አለመዘንጋትና ፣ ያስተማርዋቸውም ፣ እነሱ በሚደክማቸው ጊዜ እንዲተኳቸው ነው እንጂ እንዲነቅልዋቸው ስላልሆነ ፣ በምክር እየረዱ የመ

ተኪያውን ጊዜ ፣ በትእግሥት መጠበቅ አለባቸው ። የሥራና የባህል ልምድም የሚናቅ ፤ ነገር አይደለም ።

4 በውስጣቸው ከፍተኛ ደረጃ የተማሩ ወጣቶች ያሉዋቸው ባለሥልጣኖች ደግሞ ፣ በምክራቸውና በእውቀታቸው መጠቀምና እንደ ልጆቻቸው መቁጠር ነው እንጂ ፣ ሊነጥቅ እንደመጣ አውሬ እነሱን ማራቅ አያስፈልግም ፤

በኢትዮጵያ ሁለት የተማሩ ትውልዶች እስኪ ደርሱ ድረስ በዚህ አኳኋን በመግባባት እየሠሩ መቆየት ፣ አስፈላጊ ነው ።

## ጤና ጥበቃና ተራድኦ ፤

መንግሥት የሕዝብን ጤና ለመጠበቅ የሚያስፈልጉትን ጥንቃቄዎች ፣ አስቀድሞ ከመውሰዱም በላይ ፤ የተፈጥሮ መከራዎች በሕዝብ ዘንድ ለማድረስ የሚችሉትን ችግሮች ለማገድ ይታገላል ።

የሕዝብ ጤና ፤ ያንድ አገር የመጀመሪያ ሃብቱ ፣ ሕዝቡ ነው ።

በሽተኛና አካለ ጐዶሎ የበዛበት አገር አንድም ፍሬ ነገር ሊሠራ አይችልም ፣ ስለዚህ መንግሥት በዚህ ጉዳይ ሊጨነቅበት በቂ ምክንያት አለው ።

የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ፣ የሕዝብን ጤና ለመጠበቅ የሚያገለግሉትን ነገሮች ሁሉ በማስተባበር ለምሳሌ ፣ እንደ ሳንባ ነቀርሳና እንደ አልኰል ፣ ያሉትን መቅሰፍቶች ለማስወገድ ፣ አስፈላጊውን ያደርጋል ።

ለምሳሌ መከተብን ፣ ግዴታ በማድረግ ፣ የያንዳንዱን ሰው ጤና እየጠበቀ መላውን ሕዝብ ደግሞ ከተላላፊ በሽታ ያስጥለዋል ።

አገራችን ኢትዮጵያ ሰፊ እንደመሆኗ መጠን ፣ በውስጧ የሚኖረው ሕዝብ ቍጥሩ አነስተኛ ነው ። በግል ጤናም ረገድ ብዙዎቹ የበቃ ጥንቃቄ አያደርጉም ፣ ስለዚህ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የሕዝቡን ቍጥር ለማብዛት ብቻ ሳይሆን ጤናማ ሕዝብም እንዲሆን ጭምር ማሰብ ስላለበት ፤ የሚሞቱት ሰዎች ቍጥር እንዲቀነስ የሚወለዱት ቍጥር እየተጨመረ እንዲሄድ የሕክምና እርዳታ በሰፊው ያዘጋጃል ።

ተ ራ ድ ኦ ፤ ያለው ፣ ለተቸገረው በመመጽወት ፣ አንዱ ያንዱን ችግር ማቃለል ከጀመረ አያሌ ጊዜ ነው ።

በዛሬ ጊዜ ግን ፣ የተቸገሩትንና የተጐዱትን መርዳት ብቻ ሳይሆን ፤ ችግርና ጉዳት ራሳቸው እየጠፉ እንዲሄዱ ማድረግ የመንግሥት ፣ ፋንታ ሆኖ ስለተገኘ ፣ የችግሮች ዝርዝር እየወጣ ከመድረሳቸው በፊት መድኃኒት እንዲፈለግላቸው ይደረጋል ። ለምሳሌ ፣ ሥራ መፍታት ፣ በሽታ ፣ አካለ ጐዶሎነት ፣ እርጅና ፣ የቤተ ሰብ አባት መሞት ፣ በነዚህ ውስጥ ይቆጠራሉ ፣ ለነዚህ ጉዳቶች ስታቲስቲክ በማብጀትና ከሕዝብ መዋጮ ወይም የተራድኦ ቀረጥ በመቀበል ሕዝባዊ መተማመኛ ፣ የተባለ ድርጅት ማቋቋም ይቻላል ።

ይህ ድርጅት በሕዝብ ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ውስጥ ፣ ወይም በጡረታ ሚኒስቴር ውስጥ ሊሆን ይችላል ።

# የገንዘብ አስተዳደር ፤

<u>የገንዘብ ሚኒስቴር</u> ፣ ወጭና ገቢውን ለማስተካከል ከመድከሙም በላይ ፣ የመንግሥቱ ገንዘብ ለምን እንደሚውል በጥብቅ ይቆጣጠራል ።

<u>ገንዘብ (ፊናንስ)</u> ባላፉት ገጾች የዘረዘርናቸው ፤ መከላከል ፣ ዳኝነት ፣ ትምሕርት ፣ በጐ አድራጐት ፣ የሚያኰሩና አስፈላጊ ቢሆኑም ፣ ብዙ ገንዘብ የሚጠይቁ ተግባሮች ናቸውና ገንዘቡን ማግኘት ያስፈልጋል ።

ይህ ሁኔታ መጀመሪያ መንግሥት ገንዘብ እንዲኖረው ቀጥሎም ፣ ይህ ገንዘብ ፣ በሥርዓት እንዲተዳደር ይጠይቃል ፣ ከዚህም በቀር የመንግሥቱ ገቢው ወጭዎቹን እንዲችል ያስፈልጋል ።

እላይ እንዳልነው ሁሉ ሕዝቡ ከመንግሥቱ ፣ መከላከያ ኃይልን ፣ የውስጥ ጸጥታን ፣ ዳኝነትን ፣ ትምሕርትን ፣ ጤና ጥበቃን ፣ ጡረታን ፣ ይጠይቃል ።

መንግሥት ለሕዝቡ ይህን ሁሉ ለማዘጋጀት ፣ ገንዘብ ያስፈልገዋል ፤ ይህም ገንዘብ በነዚህ ፣ አቅዋሞች በቀጥታ ከሚጠቀምባቸው ፣ ከሕዝቡ እንዲመጡ ተገቢ ነው ። እንግዲህ አንድ ሰው ለመንግሥት ቀረጥና ግብር ሲከፍል ፣ ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት ድርጅቶች የሚፈልቀውን ፣ ጥቅም ተካፋይ ለመሆን ገንዘብ ማዋጣቱ ነው እንጂ ገንዘቡን አንስቶ ለሌላ ሰው መስጠቱ አለመሆኑን መረዳት አለበት ፤ ገንዘቡን የምንከፍለው ለራሳችን ስንል ከሆነ ለምን በሕግ ይዘው በግድ ያስከፍሉናል የሚሉ አይጠፉም ፣ እዚህ ላይ ማወቅ የሚገባ ፣ አንድ ሰው ባንድ አገር ውስጥና ባንድ ሕዝብ መካከል ሲኖር ፣ ያገሪቱን ፍሬ ሲመገብና በሌሎች ሰዎች ሥራ ሲጠቀም ፤ በማሕበሩ ውስጥ ውሉን ወዶ ገብቷል ማለት ነው ። ግብር ሲጠየቅ አልከፍልም ያለ በሕግ የሚገደደው ይህን ውል ስላፈረሰ ነው ። በቀጥታ ከግብር የሚመጡትን ሕዝባዊ ገቢዎችን የሚያስተዳድር የገንዘብ ሚኒስቴር ነውና ፣ የሚያጋጥመው ችግር እጅግ ከፍ ያለ ነው ፤ ሚኒስቴሮቹ በባጀታችን መሠረት ከፍ ያለ ገንዘብ ስጠን ብለው በሚገባ ይጠይቁታል ፤ ግብር ከፋዩ ደግሞ በዝቶብኛልና ይነቀስልኝ ስለሚል በሁለቱ መካከል የሚዋጅቅ ገንዘብ ሚኒስቴሩ ነው ። ዳኙ ግን የግብሩን ልክና ፣ አወጣጡን ወስኖ የሚሰጠው ፓርላሜንቱ ስለሆነና እሱም የንጉሠ ነገሥቱና የሕዝብ እንደራሴዎችን ፈቃድ ፈጻሚ ስለሆነ ፤ ተጠያቂነቱ በዚሁ መጠን ይቃለልለታል ።



ይህም ሆኖ የገ/ሚኒስቴር ሥራ ፣ ልዩ ሞያቸው የሆነ ፣ ጥንቁቅ ሠራተኞች ይሹታል ።

<u>ባጀትና ግምጃ ቤት ፤</u>

በመሠረቱ እዝርዝር ጉዳይ ውስጥ ሳንገባ ፣ በባጀትና በግምጃ ቤት መካከል ፣ ያለውን ዓይነተኛ ልዩነት ማወቅ

ጠቃሚ ነገር ነው ። ለዚሁም ፣ ምሳሌ እንውሰድ ፣ አንድ ሰው በመስከረም አንድ ቀን በማጥኑ ውስጥ ዜሮ ብር አለው (ምንም የለው ማለት ነው) ነገር ግን ፣ በመስከረም ወር ውስጥ የሚቀበለው ገቢ ፣ 100 ብር እንዳለው አስቦ አውቋል ፤ በዚሁ ወር ውስጥ ደግሞ ወጭው 80 ብር እንደሚሆን ገምቷል ፣ ይህን ሂሳብ ሲያደርግ ይህ ሰው ባጀቱን ወሰነ ማለት ነው ፤ በወሩ መጨረሻም 20 ብር ፣ ስለሚተርፈው ባጀቱ አጥጋቢ ነው ።

ነገር ግን ገቢውን 100 ብር ባንድ ጊዜ ሳይሆን በከፊልና በየጊዜው የሚቀበል ፣ ስለሆነ ገንዘብ የሚቀበልበትና ወጭ ፣ የሚያደርግበት ቀን ሳይገጣጠሙ ሊቀሩ ይችላሉ ። ይህን በመገንዘብ ሰውዬው የገንዘቡ አወጣጥ ከገቢው ጋራ በሚስማማ አኳኋንና ጊዜ እንዲፈጸም ለማድረግ ይሞክራል ፤ ይህን ሲያደርግ የግምጃ ቤቱን ሥራ አከናወነ ማለት ነው ።

ለምሳሌ በመስከረም 10 ቀን የ15 ብር ዕቃ መግዛት ቢኖርበት ፣ በመስከረም 8 ቀን ከሰው የሚቀበለው 20 ብር ስላለው ግዥውን ሊያደርግ ይችላል ።

ይህ ሁኔታ ምን ያስረዳል ? ሰውዬው ምንም እንኳ ባጀቱ በቂና ተራፊ ቢሆንም ፣ በመስከረም ወር ውስጥ ፣ ልዩ ልዩ የገንዘብ ሁኔታ ሊገጥመው እንደሚችል ፣ ያስረዳናል ፤ በወሩ መጀመሪያ አብዛኛውን ገንዘብ ገቢ ያደረገ እንደሆነና ፣ ከፍ ያለ ወጭም ያለበት በወሩ መጨረሻ ገደማ ሲሆን፣ ግምጃ ቤቱ ፣ በተመቸና በሰፊ ሁኔታ ላይ ሊገኝለት ነው ።



ነገር ግን ይህ ሰው በመስከረም 8 ቀን ይጠብቀው የነበረው ገንዘብ በከፋዩ ድንገተኛ ችግር ምክንያት ሳይገባለት ቢቀር፣ ላሰበው ግዥ ገንዘብ ስለሚያጣ ፣ ምንም እንኳ ባጀቱ በቂ ቢሆን የግምጃ ቤት ፣ ችግር ገጠመው ማለት ነው ፤ የግምጃ ቤት ችግር ገንዘቡ ገቢ በሆነ ጊዜ ሊጠናቀቅ ፣ ስለሚችል ፣ አላፊና የዕለት ችግር ነውና አዋኪነቱ እጅግም አይደለ ። የባጀቱ ፣ መዛነፍ ግን ይበልጥ አስቸጋሪ ነው ፣ ለወጭው የገመተው 80 ብር ሳይበቃ ቀርቶ 120 ብር ቢያስፈልገውና ገቢው ከመቶ ብር የማይበልጥ ከሆነ ፣ መውጫ ከሌለው ችግር ውስጥ ይገባል ፣ እዚህ ላይ ወይም ትርፍ ሰዓት መሥራት ወይም ከጥቅምት ባጀት ላይ መበደር ሊያስፈልግ ነው ፤ የመንግሥትም ሁኔታ እንደዚሁ ነው ። በያመቱ በገንዘብ ሚኒስቴሩ አዘጋጂነት ፣ የታሰቡት የዓመት ገቢና ወጭዎች ፣ ለፓርላሜንቱ ቀርበው ፣ አዋጭው ሕዝብ እንደመሆኑ መጠን ፣ በሕዝብ እንደራሴዎች ይፈቀዳሉ ፤ የባጀቱም አፈቃቀድ በጠቅላላው ድምር ሳይሆን በአቀራረቡ ላይ በአርእስቱ ስለሆነ ፣ በዚሁ መሠረት አንድ በአንድ ይፈቀዳልና ፣ ላንድ ጉዳይ የተወሰነው ሂሳብ ለሌላ ጉዳይ ሊውል አይችልም።የባጀት ድሬክሲዮንና የጠቅላይ ግምጃ ቤት ድሬክሲዮን በገንዘብ ሚኒስቴር ውስጥ ከፍ ያሉ ክፍሎች የሆኑት ከዚህ በላይ በዘረዘርናቸው ምክንያቶች ናቸው ።

<u>የሂሳብ ትመራመር ፤</u>

አዋጭዎች የከፈሉት ገንዘብ በተፈቀደውና በትክክለኛ መንገድ መውጣቱን ፣ መንግሥት በጥንቃቄ መቆጣጠር አለበት ። ለዚሁ ሥራ የተመደቡ የአውዲትና ፣ የሂሳብ

ኢንስፔክተሮች እየተዘዋወሩ ሂሳቡን በመመርመር ፣ የያን
ዳንዱ ሚኒስቴር ወጭም ፣ ከባጀቱ ሕግ ጋራ ተስማሚ መሆ
ኑን ይቆጣጠራሉ ።

# የሕዝብ አካላዊ ኑሮ ድርጅት

ያንድ ሕዝብ አካላዊ ኑሮ እንዲረጋገጥ ምግብ ፣ ልብስ፣
መገናኛ መከላከያና ምቾት ያስፈልገዋል ፣ እነዚህን የማይ
ታለፉ ነገሮች ለማግኘት ፣ ሰው እንዲሠራ ፣ እንዲያርስ ፣
እንዲነግድ ፣ እንዲዘዋወርና እንዲላላክ ስለሚያስፈልግ ፣
መንግሥት በልዩ ልዩ ሚኒስቴሮች አማካይነት ሕዝብን
ይረዳዋል ።

1 <u>የሕዝባዊ ኑሮ እድገት ሚኒስቴር ፤</u> የሥራውን ዘዴ
በማስተማር ሠራተኞች የሚጠበቁባቸውን ማሕበራዊ ድር
ጅቶች በማቋቋም ፣ ሕዝብን በሥራ ረገድና ማሕበራዊ ኑ
ሮን ለማሻሻል ይረዳዋል ፣ (ስለ ሕብረ ግብርና በሌላ ገጽ
ተመልከት)

2 <u>የንግድና የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ፤</u>

የንግድ ሚኒስቴር ፣ በአገሩ ውስጥ የንግድን ሥራ እየ
ተቆጣጠረ ያስፋፋል ፣ በተለይም የሸቀጦችን ዋጋ የሚወ
ስን እሱ ነው ። በየጊዜው በሚያዘጋጀውም ስታቲስቲክ መ
ሠረት አገሩ የሚያፈራውንና ለኑሮው የሚያስፈልገውን
በማመዛዘን ይረዳል ። እንደጊዜው አስፈላጊነትም ፣ ከአ



ገር የሚወጣውንና ወደ አገር የሚገባውን ሸቀጥ የሚወስን
እሱ ነው ፤ እንደዚሁም አገሪቱ ከውጭ አገሮች ጋር የምታ
ደርገውን የንግድ ግንኙነት የሚያጠናቅቅ ፣ እሱ ነው ፤

በኢንዱስትሪ በኩል ደግሞ ፣ በመንግሥት የሚተዳደ
ሩትን ልዩ ልዩ አቅዋሞች ፣ በቀጥታ ከማስተዳደሩ በቀር ፣
በአገር ውስጥ የፋብሪካዎችን ማቋቋም ያበረታታል ፣ ባለ
ፋብሪካዎች የሚያስፈልጋቸውን መሣሪያ እንዲያገኙ ይረ
ዳቸዋል ።

<u>ስለ ንግድ አጭር መግለጫ ፤</u>

<u>የችርቻሮ ንግድ ፣</u> በሰፈርና በጊዜ ረገድ ፣ ሸቀጥን ለሸ
ማቹ በዝርዝር ወዲያው የሚያስገኝለት ንግድ ነው ። የጅ
ምላ ንግድ ደግሞ በባለፋብሪካውና በቸርቻሪው ፣ መካከል
ያለው አገናኝ ነው ። ደግሞም አንዳንድ ታላላቅ የንግድ
ቤቶች የችርቻሮን ንግድ ራሳቸው አጠቃለው ይዘውታል ።

<u>ችርቻሮና ፍቹ</u> ትንሽ ነጋዴ ወይም ቸርቻሪ ማለት ፣
በጥቂት በጥቂቱ ሸቀጡን በቀጥታ ለያንዳንዱ ሸማች የሚ
ያቀርብና አብዛኛውን ጊዜ ብቻውን ወይም ቢበዛ ፣ ባንድ
በሁለት ሰው እየተረዳ የሚሠራው ነጋዴ ነው ። ፍሬ ነጋዴ፣
ባለ ቡና ቤት ፣ ሸቀጣ ሸቀጥ (አረብ ቤት የምንለው) እነዚህ
ሁሉ በዚህ ውስጥ ይቆጠራሉ ፤

<u>የጅምላ ንግድ ፤</u> እንዳየነው ሁሉ ችርቻሮ ሸቀጥን ለሸ
ማቹ ያቀርብለታል ፤ ሸቀጡስ ፣ ወደ ቸርቻሪው በምን አኳ

የሚያስፈልጋቸውን ደን እስከ መትከልም ደርሰው ነበረ ። ይህ ዘዴ ለጊዜው ተስማሚ ይመስላል እንጂ ፤ ጠቃሚነቱ የተረጋገጠ አይደለም ።

ባለትልቁ ፋብሪካ ሰው ፣ ጉማውን ፣ መስቷቱን ፣ ባትሪውን ፣ ራሱ የሠራ እንደሆነ ፣ ራሱ ለሚያወጣቸው መኪናዎች ብቻ ስለሆነ በብዛት ሊሠራ ካለመቻሉም በቀር ይህ የተወሰነ ሥራ ልዩ ሞያው ባለመሆኑ አጠናቆ ሊያዘጋጀው አይመቸውም ፤ በብዛትም ስለማይሠራው ፣ ዋጋው ከፍ ይልበታል ፤ በተረፈ በዚህ ሥራ የሚኖሩትን ታናናሽ ኢንዱስትሪዎች ስለሚገድል ፣ በብዙ አገሮች መንግሥት በሕግ ይከለክለዋል ።

ባለትንሽ ኢንዱስትሪው ግን የሚሠራው ያችኑ ዕቃ ብቻ ስለሆነና ፣ ለልዩ ልዩዎቹም ፣ የአቶሞቢል ፋብሪካዎች ስለሚሸጥ ፣ በዓይነትም ጥሩ በዋጋም ርካሽ አድርጐ ሊያዘጋጅ ይችላል ።

ሁኔታ የሚፈጥረው ሞኖፖል ፤ አንድ ነጋዴ ተወዳዳሪዎቹን ሁሉ ሊያጠፋ የቻለ እንደሆነ ፣ ወይም ራሱ የሥራው ዓይነት ካንድ ከታላቅ ፋብሪካ በቀር ሌላ ሊያከናውነው የማይቻል ሆኖ ሲገኝ ፣ መሥራቱና መሸጡ ያንድ ብቻ ልዩ መብት ይሆናል ፤ ይህም ሁኔታ ሞኖፖል ይባላል ፤ ይህ ሞኖፖል በሕግ ተፈቅዶ ወይም በውል ተሰጥቶ ሳይሆን ፤ የሌሎቹ ነጋዴዎች መውደቅ ያፈራው ስለሆነ ሁኔታው የፈጠረው ሞኖፖል ይባላል ።



ነጋዴዎች በልዩ ልዩ ዘዴ ይህ ሁኔታ እንዲፈጠር ያደርጋሉ ። ለምሳሌ ፣ ከፍ ያለ የገንዘብ ኃይል ያለው አንድ ታላቅ ፋብሪካ ፣ ዕቃውን ለጊዜው በኪሣራና በዝቅተኛ ዋጋ በገበያ መሸጥ ይጀምራል ፤ እንደሱ ሃብት የሌላቸው ተወዳዳሪዎቹ በኪሣራ እንደሱው እንዲሸጡ ወይም ዕቃቸውን ታቅፈው እንዲቀሩ በማድረግ ፣ ጨርሶ ያከሥራቸዋል ።

በዚህ አኳኋን ተወዳዳሪዎቹ ከሰረው ገበያውን ሲለቁለት ንግዱን በሞኖፖል ይይዝና ባሰኘው ዋጋ በመሸጥ ፣ በመጀመሪያ ደርሶበት የነበረውን ኪሣራ እጥፉን ለመመለስ ይችላል ።

ይህ አሠራር በእንግሊዝኛ ደምፒንግ ይባላል ። ደምፒንግ በመንግሥታት መካከልም ይደረጋል ፤ በዚህ ጊዜ በደምፒንግ ለመጠቀም የሚፈልገው መንግሥት ፣ ያገሩን ፋብሪካዎች በገንዘብ በመርዳት በውጭ አገር ገበያ ከተወዳዳሪዎቻቸው ባነሰ ዋጋ እንዲሸጡ ፣ ያደርጋል ። የቤንዚን ገበያ በዓለም ላይ በዚሁ ዘዴ ሰብስበው በያዙት በጥቂት ማሕበሮች እጅ ብቻ መገኘቱ የታወቀ ነው ።

የመንግሥት ሞኖፖሎች ፤ አንዳንድ ጊዜ ፣ መንግሥት ላገር ኤኰኖሚካዊ ጥቅም የሚበጅ መስሎ ሲታየው አንዱን ዓይነት ዕቃ ራሱ ብቻ ለማውጣትና ለመሸጥ የሚያስችለው መብት በሕግ ያስወስናል ፤ ይህም ሕጋዊ ወይም የመንግሥት ሞኖፖል ፣ ይባላል ።

ለምሳሌ የኢትዮጵያ መንግሥት የትምባሆን ሞኖፖል ይዟል ፤

<u>ባለአክሲዮን ማሕበሮች</u> ፤ አንዳንድ የኢንዱስትሪና የንግድ ግብርናዎች ፥ ባንድ ግለሰብ ሃብት ብቻ ሊንቀሳቀሱ የማይቻልበት ጊዜ አለ ። የድርጅቱ ታላቅነት ፥ ያንድ ሰው ሃብት ብቻ ሊያንቀሳቅሰው ፥ የማይፈቅድ ይሆናል ። በዚህ ጊዜ ዋናውን ገንዘብ ብቻ ሰዎች ያዋጣሉ ። የሚያዋጡትም ገንዘብ እንደየችሎታቸው ስለሆነ ጥቂትም ብቻ የሚያገቡ አሉ ። ባወጡትም ገንዘብ መጠን ፥ አንድ ወይም ብዙዎች አክሺን የተባሉ ሰነዶች ይሰጧቸዋል ። እያንዳንዱ አክሺን የዋናው ገንዘብ አንድ መቶኛ ወይም አንድ ሺየኛ ሊሆን ይችላል ። ለምሳሌ ዋናው ገንዘብ ሺ ብር ቢሆንና ለሁሉም መቶ አክሺኖች ቢመድቡለት እያንዳንዱ አክሺን አስር ብር ማውጣቱ ነው ።

አንዱ አክሺንም የዋናው ገንዘብ አንድ አሶረኛ መሆኑ ነው ። አክሲዮኖቹ ሊሸጡ ሊለወጡ የሚችሉ ፥ ከማሕበሩ ትርፍም ለመካፈል መብት የሚሰጡ ሰነዶች ናቸው ። አክሺኖቹ እንደ ቍጥራቸው መጠን ለባለቤቱ የሚያሶገኙት ትርፍ ድርሻ ይባላል ።

በአክሺን የተቋቋሙ ማሕበሮች ባሶፉት ገጾች የተነተናቸውን ፥ ታላላቅ ባለሃብት ኢንዱስትሪዎች ኃይላቸውን አላግባብ በመዘርጋት የሚያደርጉትን ሞኖፖል የሚያሶታግሱ አቅዋሞች ናቸው ።

ሥራውም ያንድ ሰው ወይም ያንድ ቤተ ሰብ ልዩ መብት በመሆን ፈንታ አነሶተኞች ቆጣቢዎች ገንዘባቸውን



ከመቅበር ይልቅ አክሺን ገዝተው ስለሚያሠሩት ፥ ለሕብረሰብ የሚሰጠው ጥቅም በጣም ከፍ ያለ ነው ።

በኢትዮጵያ የወንጂ ሱኳር ማሕበር ፥ የድሬዳዋ ጥጥ ማሕበር ፥ ሌሎችም በአክሺን የሚሠሩ ብዙ የንግድና የኢንዱስትሪ አቅዋሞች አሉ ።

## የእርሻ ሚኒስቴር

የእርሻ ሚኒስቴር ዓይነተኛ ተግባሩ ፥ የኢትዮጵያ ምድር ፍሬ ለመሶጠት የምትችልበትን ዘዴ መፈለግና ማጠናቀቅ ፤ እንዲሁ ም ያገሪቱን የወሃና የደን ሃብት የመጠበቅና የማስፋፋት አደራ የተጣለበት አቅዋም ነው ፤ (ስለሕብረ ግብርና በተከታዮቹ ገጾች እንገልጻለን ።)

## የሥራና የመገናኛ ሚኒስቴር

ባለፉት ገጾች የዘረዘርናቸው ፥ የንግድ ፥ የኢንዱስትሪ፥ የእርሻ ሥራዎች ሁሉ ተገቢ መገናኛ ከሌለ ደንበኛ ጥቅም ሊያሶገኙት ይችሉም ። መገናኛ ሲባልም ፤ መንገዶች ፥ ሐዲዶች ፥ ወሃዎች ፥ ናቸውና ባገልግሎት ላይ እንዲውሉ ፥ ድልድዮቹ ፥ ግደቦች ፥ ኤሌክትሪክ ሞተሮችና መሶመሮች ማዘጋጀት አስፈላጊ ነው ። ስለዚህ ሥራንና መገናኛን ባንድ ሚኒ

ስቴር ማጠቃለሉ አስፈላጊና ተገቢ ሆኖ ተገኝቷል ። የንግድ መርከቦችና የንግድ አየር መንገዶች የሚተዳደሩት በዚሁ ሚኒስቴር ውስጥ ነው ።

ማንኛት ፥ መሸጥ ፥ መለወጥ ፥ መዋዋል ፥ ይህን የመሳሰሉት ነገሮች አሳብን በጽሑፍ ወይም በቃል ለማስተላለፍ የሚቻልበትን ዘዴ ስለሚጠይቁ ፥ ለሕዝብ አካላዊ ኑሮ አስፈላጊ ከሆኑት አቅዋሞች ከዋናዎቹ አንዱ ፥ የፖስታ ፥ የቴሌግራፍና ቴሌፎን ሚኒስቴር ነው ።

በኢትዮጵያ የስልክና የሬዲዮ ግንኙነቶችን የሚያከናውን ፥ የቴሌኰሙኒኬሺን ቦርድ ነው ፤ ፍቹም ፥ ቴሌ ሩቅ ማለት ሲሆን ፥ ኰሙኒኬሺን መገናኛ ነውና የሩቅ ማገናኛ (አቀራራቢ) ልንለው እንችላለን ። በተረፈ ፥ በልዩ ልዩ ከተሞች የሚኖሩ ሰዎች ገንዘብ በፖስታ ለመላክ የሚችሉበትን ሐዋላ እየተባለ የሚጠራውን አስደናቂ የሆነ ዘዴ የሚመራ ፖስታ ሚኒስቴር ነው ።

## የሚኒስቴሮች ተባባሪነት ፤

ከዚህ በላይ የጠቀስናቸው ሚኒስቴሮች ለየራሳቸው የተወሰነ ሥራ ቢኖራቸውም ፥ በአሠራር ረገድ በብዙ መንገድ ይገናኛሉ ።

ለምሳሌ ፥ ስለቤንዚን እናስተውል ። ቤንዚን ለማስመጣት የውጭ አገር ገንዘብ ያስፈልጋል



(ገንዘብ ሚኒስቴር) እንዲሁም ከባለ ቤንዚኖቹ አገሮች ጋራ መስማማት ያስፈልጋል ፤ (ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር) ፥ ቤንዚኑን ለየሥራው ማከፋፈል ያስፈልጋል (መገናኛ ሚኒስቴር) ደግሞም የሚመጣውን ቤንዚን መጠን መወሰንና እንዲገባ መፍቀዱ የንግድሚኒስቴር ሥራ ቢሆን ቤንዚን በብዛት ባልተገኘ ጊዜ ፥ በከሰል ወይም በእንጨት እሳት መጠቀም ስለሚያስፈልግ እርሻ ሚኒስቴርን ያገባዋል ።

በተረፈም የቤንዚን ማነስና መብዛት ፥ በመንገድ ፥ በባሕር ፥ በአየር የሚደረገውን ግንኙነት ሊያበዛውና ሊያሳንሰው ስለሚችል ፥ የሥራና የመገናኛ ሚኒስቴርን ፥ ፖስታ ሚኒስቴርንም ጭምር ማሳሰቡ አይቀርም ፤

ይህ ባንድ ጉዳይ የብዙ ሚኒስቴሮችን መተባበር የሚጠይቅ ሁኔታ ለአርእስቱ በቂ ምሳሌ ነው ፤

## በሕብረት የሚፈጸሙ ሥራዎች

### ወ ይ ም ሕ ብ ረ ግ ብ ር ና

ለማመንጨትም ሆነ ፥ ለመግዛት ፥ ለመበደርም ሆነ ለማበደር ፥ አመንጭው ፥ ገዥው ፥ አበዳሪው ፥ ተበዳሪው ለማግኘት ከሚመኙት ትርፍ እያንዳንዱ ሰው ለመቆጠብ ፥ እንዲችል ፤ ሕብረ ግብርና ይፈቅድለታል ፤

የሕብረግብርና መሠረታዊ ፍች ፤ ቃሉ ራሱ እመ ጣጡ ሕብረ ፥ እብሮ ፥ ግብርና ሥራ ማለት ስለሆነ ፥ ተባ ብሮ መሥራትን የተመረኰዘ ነው ።

ለምሳሌ እንድ የሰርዲን ፋብሪካ እንውሰድ ፥ የሚሠ ራው ባለቤቱ ትርፍ ያገኝበታል ። ነገር ግን ፥ በውስጡ ያ ሉት ሠራተኞች ላንድ ባለቤት ከመሥራት ይልቅ እራሳ ቸው በማሕበር ተቋቁመው ያመነጩ እንደሆነ ፥ ትርፉን እራሳቸው ይካፈላሉ ።

ሰርዲኑ በቆርቆሮ ሆኖ ከተሠራ በኋላ ፥ ተመጋቢው ገኙ ከነጋዴ ዘንድ ይገዛል ። ነጋዴው ፥ ትርፍ ያገኝበታል ማለት ነው ። ነገር ግን ገዥዎቹ በማሕበር ተቋቁመው ፥ ሰርዲኑን ፥ በብዛት አንድ ጊዜ ገዝተው የተከፋፈሉ እንደ ሆነ ፥ አትራፊዎቹ እነሱ ይሆናሉ ፤ ቸርቻሪው ከነሱ ይበላ የነበረውን ትርፍ ያድናሉ ማለት ነው ። እነዚህ ሁለቱ እ ጭር ምሳሌዎች ፤ የሕብረ ግብርናን ሥራ በማመንጨትም ሆነ ፥ በመግዛት ሊፈጸም መቻሉን ያስረዱናል ፤ ስለዚህ ፥ የማመንጨት ሕብረ ግብርና ፥ የመግዛት ሕብረ ግብርና የተባሉ ሁለት ዓይነቶች አሉ ።

ደግሞም አንድ ቤት ለማሠራት ገንዘብ ያስፈለገኝ እንደሆነ ፤ ከአንድ ባንክ ፥ በወለድ እበደራለሁ ። ግን ፥ ቤት መሥራት የምንመኝ ብዙዎች የሆንን እንደሆነ ፤ ተቀማጭ፤ ገንዘባችንን ፥ ባንድ እናደርግና ፥ ከተጠራቀመው ዋና ላይ ፥ ለያንዳንዳችን የቤት መሥራት ተራችን ሲደርስ የሚረዳን ገንዘብ በብድር ይሰጠንና በዝግታ እንከፍላለን ፥ የተበዳሪ



ዎቹ ሕብረ ግብርና ይባላል ፤ ያገራችን ዕቁብ በዚህ መልክ የተቋቋመ ነው ።

ልዩነቱ ሕብረግብርናው በየተራው ሲያከፋፍል ፥ ዕ ቁብ ግን በዕጣ ያድላል ፤ በመሠረቱ ግን ፥ የሁለቱም ዓላማ ጥቂት ገንዘብ በማዋጣት ከፍ ያለ ገንዘብ ማከማቸትና እያ ንዳንዱ ሰው ባንድ ጊዜ ጠርቀም ያለ ገንዘብ አግኝቶ በሥራ ላይ አውሎት በጥቂት በጥቂቱ እንዲከፍል ለማድረግ ነው ።

<u>የማመንጨት ሕብረግብርና</u> ፤ የዚህ ዓይነት ሕብረግብ ርና በብዙ መንገድ ሊዘጋጅ ይችላል ። ለምሳሌ ፤ የወይን ተክል ያላቸው ብዙ ገበሬዎች ፥ በሕብረግብርና ፥ ይቋቋ ሙና የወይን ፍሬያቸውን ባንድ ቀላቅለው ፥ ወይን ጠጅ በብዛት በማውጣት በጅምላ ፥ ለመሸጥና በቀጥታ ለማት ረፍ ይችላሉ ።

በተለይ ባገራችን የወተት ነጋዴዎች ሥራ በጣም ደካማ ነው ። እያንዳንዱ ሰው ፥ አንድ አስር ሊትር ወተት በቆርቆሮ ተሸክሞ ብዙ ኪሎ ሜትሮች አቋርጦ ይመጣና አንድ ሁለት ብር ያህል አትርፎ ይመለሳል ፤ በዚህ አኳኋን ምንም ፥ ጊዜ ቢሆን ኑሮውን ለማሻሻል አይችልም ። ባንድ አጠራቅመው ፥ የሚናጠውንም ንጠው ቅቤ በብዛት ቢያ ወጡ የቀረውንም በካሚዎን ፥ እያስጫኑ ከተማ ሄዶ እንዲ ሸጥ ቢያደርጉ ፤

እንደኛ ፥ የመመላለሱን ሥራ ጥቂቶች ሰዎች ብቻ ስለሚፈጽሙት የቀሩት ከጧት እስከ ማታ ሥራ ከመፍታት ይድኑና ሌላ ተግባር ሊያከናውኑ ይችላሉ ።

ሁለተኛ ፥ ማሕበሩ ለሁሉም ደንበኛ ዋጋ ወስኖስለሚሸጥ እርስ በርሳቸው በዋጋ በመወዳደር በዝቅተኛ ዋጋ ከመልቀቅ ይድናሉና የበለጠ ጥቅም ያገኙበታል ።

ሶስተኛ ፥ እያንዳንዱ ወተት ሻጭ ወደከተማ ሲመጣ ፥ ለአቶቡስ ፥ ለምግብ ለመጠጥ ከሚያወጣው ወጭ ሁሉ ይድናል ፤ በጠቅላላው በሕብረግብርና ማመንጨት ፥ ለማሕበረተኞች ከፍ ያለ ጥቅምና በመተባበር ስጋትን ከያንዳንዱ ላይ ለማራቅ ይጠቅማል ።

የግዥ ሕብረግብርና ፥ በላይኞቹ መስመሮች የግዥ ሕብረግብርና የሚሰጠውን ፥ ጥቅም ዘርዝረናል ፤ በመሠረቱ እነዚህ ማሕበሮች ፥ በችርቻሮ የሚሸጥባቸው ሱቆችናቸው ። አንዳንዶቹ አንድ ዓይነት ሸቀጥ ብቻ ይሸጣሉ ፤ አንዳንዶቹ ደግሞ ፤ ዳቦም ፥ ሥጋም ፥ የወጥቤት ዕቃም ፥ ልብስም ይሸጣሉ ፤

ድርጅታቸው ቀጥሎ እንደተመለከተው ነው ። ለምሳሌ ባንድ መንደር የሚኖሩ ሰዎች ፥ የምግብ ዕቃ የሚሸጥበት ሱቅ አዋጥተው ያቋቁማሉ ፤ ማሕበረተኞች ሁሉ አንድ የተወሰነ ገንዘብ ያወጡና ሱቁ ፥ አንድ ካፒታል እንዲኖረው ያደርጋሉ ፤ ሱቁ ከፋብሪካው በቀጥታና በጅምላ ፥ ልዩ ልዩ የምግብ ዓይነቶች በደህና ዋጋ ይገዛና ማሕበረተኛ ለሆኑት ሁሉ በተሰማሙበት ጥሩ ዋጋ ይሸጥላቸዋል ፤ በዚህ ጊዜ ችርቻሪ ከሚበላቸው ትርፍ ዳኑ ማለት ነው ፤ ደግሞም ፥ ሱቁ ለማሕበረተኞቹ በችርቻሪ ዋጋ ይሸጥላቸውና



የተገኘውን ትርፍ ባመቱ መጨረሻ በገዙት ሸቀጥ መጠን እየታሰበ ይከፋፈላሉ ።

ወይም ለማሕበረተኞቹ በዝቅተኛ ዋጋ ፥ ማሕበረተኛ ላልሆኑት በገበያ ዋጋ እየሸጡ የተገኘውን ትርፍ እላይ በተባለው ዘዴ ይከፋፈላሉ ፤ ለምሳሌ አንድ ቤተሰብ የሺብር ሸቀጥ ገዝቶ እንደሆነ ፥ መቶ ብር ትርፍ ቢደርሰው ፥ የአምስት መቶ ብር ሸቀጥ የገዛው ደግሞ ፥ ሃምሳ ብር ማለትም ግማሹ ይደርሰዋል ማለት ነው ።

በጠቅላላው ሰዎች በሕብረግብርና በማመንጨት ፥ በመግዛት ፥ በመበዳደር የኑሮአቸውን ደረጃ ለማሻሻል ስለሚያስችላቸው ጉዳዩ በቀጥታ ፥ የሕዝባዊ ኑሮ እድገትን የሚመለከት ነው ። ይህ ሚኒስቴር ፥ በየስፍራው ሕብረግብርናን በማቋቋም ላይ እንደሚገኝ ሁላችንም እናውቃለን ።

## የግል ሃብትን ሕዝባዊ ስለማድረግ

የንግድ ወይም የኢንዱስትሪ ኦቅዋሞችን ፥ ከግል ወይም ከማሕበራዊ ባለቤቶች ላይ አዛውሮ ሕዝባዊ ሃብት ማድረግን ብዙዎች ሲደግፉት አንዳንዶች የሚቃወሙት አሉ ።

ከሁሉ አስቀድመን ፥ በቃል ትርጉም እንዳንሳሳት ፥ ከዚህ ቀጥሎ የተመለከተውን እንወቅ ።

በአገራችን በተለመደ አነጋገር ፣ ምድር ባቡር የመንግሥት ነው ይባላል ፣ ይህ በመሠረቱ ስሕተት ነው ፣ መንግሥት አገርን ያስተዳድራል እንጂ ሃብት ወይም ንብረት የለውም ፣ ስለዚህ ፣ ምድር ባቡር ሕዝባዊ ሃብት ነው ፤

ይህ የሕዝባዊ ንብረት ጽሕፈት ቤት ነው ፣ ማለት ይገባናል ። ማንኛውም መንግሥት የያዘው ንብረት የኢትዮጵያ ሕዝብ ሲሆን ፣ በሕዝቡ ስም መንግሥት ያስተዳድራል፣ እንጂ የመንግሥት አይደለም ፣ አንድ ንብረት የመንግሥት ነው ከተባለ ፣ የመንግሥት ፣ ሠራተኞች ሃብት ነው እንደማለት ይሆናልና ፣ የመንግሥት ንብረት ሲባል መንግሥት የሚያስተዳድረው ሕዝባዊ ንብረት ማለት ነው ። ይህን ከገለጽን በኋላ ፣ ወደዋናው ጉዳይ እንመለስ ።

<u>የጉዳዩ ሁኔታና መነሻው ፤</u> ለምሳሌ ለሕዝብ ጠቅላላ ሕይወት አስፈላጊ የሆነ ፣ አንድ አቅዋም አለ ። ይህ አቅዋም ፤ ያንድ ወይም የብዙ ነጋዴዎች ንብረት ፣ በመሆን ፈንታ የሕዝቡ የጋራ ንብረት መሆን አለበት ሲባል ፤ አቅዋሙን ሕዝባዊ ንብረት ማድረግ ነው ። የጥርስ ቡሩሽ ወይም የጠጉር ማበጠሪያ ፋብሪካዎች ፣ ለሕዝቡ ጠቅላላ ሕይወት ፣ የማይታለፍ አስፈላጊነት ስለሌላቸው ፤ ፋብሪካቸውን ማንም ሰው ቢይዘው ግድ የለም ። ነገር ግን የምድር ከሰል ፣ ኤሌትሪክ ፣ ምድር ባቡር ሕይወታዊ ድርጅቶች ስለሆኑ ፣ ሕዝባዊ መሆን አለባቸው ። በሞራልም ረገድ ፣ ከአገሪቱ ታሕተ ምድር የሚወጣውን ከሰልና ብረት ወይም ከፏፏቴዎችዋ ፣ የመነጨውን ኤሌትሪክ ፣ ለዝቅተኛዋም ጐጆ ቢ



ሆን ግድ አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ፣ አንድ ወይም ብዙ ነጋዴዎች ሊነግዱባቸውና ሊያተርፉባቸው ፣ ተገቢ አይደለም ፤

በፖለቲካ ረገድ ደግሞ ፣ የምድር ከሰልን ፣ ኤልትሪክን ፣ ምድር ባቡርን ፣ የመሳሰሉ ፣ ኃይሎች በጥቂት ሰዎች እጅ ማድረግ ፣ እንደፈቀዱ ፣ ሊያቆሙት ፣ ሊቀንሱት ፣ ዋጋውን ሊያወጡትና ሊያወርዱት ስለሚችሉ ፣ የመንግሥትን ሥራ አመራር በኤኰኖሚ ጭቆና ሊያሰናክሉት ይችላሉ ማለት ነው ።

በሕዝባዊ አገልግሎት ረገድ ደግሞ ፣ እንደዚህ ያሉት አቅዋሞች የሚመሠረቱት ፣ ለጠቅላላው ሕዝብ አገልግሎት እንጂ ፣ ለአቋቋሚዎቹ ማትረፊያና መደሰቻ አይደለም።

ማንኛውም የግል ንግድ ፣ በትርፍ ሕግ ላይ የተመሠረተ ነው ። ትርፍ የሚጠብቅ ነጋዴም ፣ ሥራው የማያተርፈው ከሆነ ፣ ምንም እንኳ ለሕዝብ አስፈላጊ ፣ ቢሆን የግዴታ ማቆሙ አይቀርም ።

ሁለት ምሳሌዎች እንውሰድ ፣ አንድ ሐኪም ፣ የስልክ መስመር ባለው መንገድ ዳር ከተማ ውስጥ ይኖራል ፣ ደግሞ አንድ ሌላ ሐኪም ከስልኩ መስመር ሁለት ኪሎሚትር ርቆ ይኖራል ፣ ሁለቱም ሐኪሞች ለሕዝብ አገልጋዮች ናቸው ። የስልኩ ባለቤት ነጋዴ ከሆነ ፣ በመስመሩ ዳር ለሚገኘው ሐኪም በርካሽ ዋጋ ስልክ ሊያገባለት ነው ፤ ያኛው ግን ርቀቱ የሚያስከትለውን ፣ ወጭ በተጨማሪ ካልከፈለ ስልክ ላያገኝ ነው ፣ በመሠረቱ ደንበኞቹ ሩቅ የሚገኙበት ፣

የዚህኛው ስለሆነ ስልክ ይበልጥ የሚያስፈልገው ለሱ ነው። ስልኩ ግን ፣ ሕዝባዊ ሃብት የሆነ እንደሆነ ፣ ለሕዝብ በሚያገለግሉ ነገሮች ላይ ልዩነት ስለማይደረግ ለሁለተኛው ሐኪም የሚያስፈልገውን ተጨማሪ የፖስታ ሚኒስቴር ከባጀቱ አውጥቶ ፣ ይችልለታል ። ሁለተኛው ምሳሌ ፤ ሁለት ወረዳዎች በሕዝብም ብዛት በእርሻም ልማት እኩል ፣ የሆኑ አሉ ። ግን አንደኛው ወረዳ ለጥ ባለሜዳ ላይ ሲገኝ ሁለተኛው ደግሞ ፣ በኰረብታዎች ተከቦ ይገኛል ።

በትርፍ ሕግ የሚመራ ድርጅት ብዙ ወጭ ለማይጠይቀው በሜዳ ላይ ለሚገኘው ወረዳ ባቡር ሲያገባ ፣ ለሁለተኛው ግን ገንዘብ ለመቆጠብ ሲል ሳያገባለት ሊቀር ነው ።

የሕዝባዊ አገልግሎት መሠረታዊ ደንብ ግን ፣ በሁለቱም ወረዳ የሚገኙት ሕዝቦች በምድር ባቡር እኩል እንዲጠቀሙበት ያስገድዳልና የምድር ባቡር መሥሪያ ቤት ባጀቱን አቻችሎ ለሁለቱም ምድር ባቡር ማግባት አለበት ።

በመሠረቱ ያንዳንድ ኢንዱስትሪዎች ሕዝባዊ ሐብት መሆን ፣ በረከቱ ለአገረሰቡ በትክክል እንዲደርሰው የሚረዳ ዘዴ ነው ።

አንዳንድ ተቃዋሚዎች በሕገ መንግሥቱ የግል ንብረት እንዲጠበቅ ያዛልና ከግል ወስዶ ሕዝባዊ ማድረግ የመሠረቱትን ሰዎች አላግባብ መጉዳት ነው ይላሉ ። ነገር ግን ሕገ መንግሥቱ ደግሞ ፣ ለጠቅላላው ሕዝብ ጥቅም ከሆነ ፣ የማንኛውንም ሰው ንብረት አስቀድሞ ትክክለኛ ግምት ከፍሎ ለመውሰድ መፍቀዱን የዘነጉት ይመስላል ።



ም ዕ ራ ፍ 6 ፤

# የአገረሰብ መብትና ተግባሮች

በሕገ መንግሥቱ በሶስተኛው ምዕራፍ ስለሰው መብቶችና ተግባሮች ይመለከታል ፤ ያንድ አገር ሕዝብ በጠቅላላው በተለይም እያንዳንዱ አገረሰብ መብቱንና ተግባሩን ጠንቅቆ ካላወቀ ፣ ለሕብረሰብ ፣ ጠቃሚ ሆኖ ሊገኝ አይችልም ፣ ምሳሌውም ገንዘብ ሳያገባ ባዶ እጁን በንግድ ማሕበር ውስጥ ሊሻረክ እንደሚመኝ ሰው ነው ፤ ስለዚህ የሕገ መንግሥቱን ልዩ ልዩ አንቀጾች በተራ በመጻፍና ፍቻቸውን በመዘርዘር አንባቢው በበለጠ አኳኋን ሊረዳቸው እንዲችል ለማድረግ ሞክረናል ።

ሕገ መንግሥቱ ፣ በአንቀጽ በአንቀጹ የሰውን መብት ሲዘረዝር ፣ ስለነጻነትና ፣ ስለእኩልነት ፣ መብት ይናገራል ፤ እንዲሁም ስለተግባሩ ያስረዳል ፤ ስለዚህ እኛ ምዕራፋችንን በሁለት ላይ ከፍለን ማለትም ፣ ነጻነትንና እኩልነትን ፣ አስፋፍተን እንገልጻለን ።

የሰውን መብት ለማሶገኘት የተደረገ ትግል ፣ ከሰው ታሪክ ጋራ የቆየና ያረጀ ነው ።

የሕግ ሁሉ መሠረት የሆነው ደካማን ከኃይለኛ ጭቆና የማስጣል ዓላማ ነው ።